# የብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ የአደረጃጀትና የአሰራር መመሪያ

(የፀደቀ)

አዲስ አበባ

ጥር 2016 ዓ.ም

## መግቢያ

በብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ መተዳደሪያ ደንብ ላይ እንደተገለጸው ሊጉ ከፓርቲው የሚቀዳ የብልጽግና ወጣቶች አደረጃጀት ነው፡፡ ህብረተሰባዊ ለውጥን የማፋጠን፤ የወቅቱን መድረክ ተልዕኮ ተገንዝቦ በብቃት የመፈፀም፤ ሁሉንም ወጣቶች በጋራ አላማ የማሰለፍ፤ የትግል መድረክ ሆኖ የማገልገል፤ እና ጥቅሞችን የማጣጣም ቁልፍ እና ወሳኝ ተልዕኮ ይዞ የተቋቋመ የፖለቲካ አደረጃጀት ነው፡፡ ሊጉ ያነገባቸው አላማዎች የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊና የፖለቲካ ብልጽግና በመሆናቸው በተግባር ላይ ከዋሉ ወጣቶች ከሚገኙበት ኋላቀርነትና ድህነት አላቆ ለፍትህ፣ ለእኩልነት፣ ለዲሞክራሲና ለብልፅግና ያበቃቸዋል፡፡ የብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ ወጣቶችን በሀገራችን በሚካሄደው ልማት ንቁ ተሣታፊና ከሚገኘው ኢኮኖሚ እድገት እኩል ተጠቃሚ መሆናቸውን ማረጋገጥ፤ የወጣቶችን ማሕበራዊ ተሣትፎና ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ፤ ወጣቶችን ዝቅ አድርገው

የሚመለከቱ አስተሣሰቦችና ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን እንዲሁም የወጣቶችን የራሳቸውን የዝቅተኛነት አመለካከት ማስወገድ፤እና ወጣቶች በየደረጃው የፖለቲካዊ ተሣትፎና የውሣኔ ሰጪነት ሥልጣን እንዲኖራቸው በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታና በህገ-መንግስቱ ዙሪያ ዘላቂ ተሣታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ ላይ በማተኮር ማታገል ይገባናል፡፡ በመሆኑም ወጣቶች የራሳቸውን ተሳትፎና ተጠቃሚነት በማረጋገጥ ሂደት ስትራቴጅክ ሀይል መሆናቸውን በመገንዘብ ግንባር ቀደም ሚና መጫወት እንዲችሉና የብልጽግና ፕሮግራሞችን በተግባር ላይ ለመዋል እንዲቻል በሁሉም ደረጃ የሚሠራ አሠራርና አደረጃጀት መመሪያ ኖሮት በሙሉ አቅሙ መረባረብ ይኖርበታል፡፡

የብልፅግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ ተልዕኮው እና አሰራሩ ወጥነት እንዲኖረው እና አሁን ከደረስንበት የዕድገት ደረጃ በመነሳት በየደረጃ ያለውን የአመራር አካላት አደረጃጀት፤ ተልዕኮ እና አሰራር ለመወሰን የሚያስችል መመሪያ አዘጋጅቶ ሥራ ላይ ማዋል አሰፈላጊ በመሆኑ፤ የሊጋችንን ተልዕኮ እና የፓርቲያችንን ውሳኔዎችንና አቅጣጫዎችን ተግባራዊ ለማድረግ እና ከሂዴቱ የወጣቶችን ተሳታፊነት እና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የሚያስችል የሊግ አደረጃጀት እንዲኖር ለማድረግ የሚያስችል የሊጉ ህገ ደንብ በሚያመላክተው መሰረት፤ የአሰራር እና የአደረጃጀት መመሪያ ከሊጉ ዋና ጽ/ቤት ጀምሮ እስከ ቀበሌ ድረስ ያለው አደረጃጀት እንዴት ተሳስሮ እና ተናቦ መሄድ እንዳለበት የሚያሳይና በጋራ በመደጋገፍ የሊጉን ተልዕኮና የፓርቲውን ተልህኮ ለማሳካት በሚያግዝ መልኩ ማዘጋጀት በመታመኑ፤ በየደረጃው ያለው የሊጉ አመራር እና አባል በቀላሉ ለመጠቀም እንዲያስችለው ለማድረግ ከዚህን በፊት የተዘጋጀውን መመሪያ መነሻ በማድረግ አሁንም የሚታየውን ወጥነት የጎደለውን አደረጃጀት ለመፈተሽ እና በወጥነት ለማስተካከል እንዲቻል ይህ መመሪያ ተዘጋጅቶዋል፡፡

## ፩. አጭርርዕስ፡

ይህ መመሪያ የብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ አደረጃጀትና አሰራር መመሪያ ቁጥር....../፳፻፲፯ ዓ.ም' ተብሎ ሊጠራ ይችላል፡፡

## ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1) **"ሊግ"** ማለት የብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ ማለት ነው፡፡
2) **"የሊጉ የበላይ ኃላፊ"** ማለት በማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት የተመረጡ ፕሬዝደንት እና ምክትል ፕሬዝደንቶች፣ የሊጉ ሥራ አስፈጻሚና የሊጉ ዋና ጽ/ቤት እንዲሁም የክልል ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ኃላፊዎች ናቸው፤
3) **"አመራር"** ማለት በሊጉ መዋቅራዊ አደረጃጀት መሠረት በተለያየ እርከን ደረጃ የሚገኙ አስፈፃሚዎችን ነው፡፡
4) **"ቅ/ጽ/ቤት"** ማለት ከክልል እስከ ቀበሌ ያለው የሊጉ መዋቅር ናቸው ፡፡
5) **"አባላት"** ማለት በብልጽግና ፓርቲ የወጣቶች ሊግ መተዳደሪያ ደንብ መሰፈርት መሰረት

የተመለመሉና በሊጉ የተደራጁ ወጣቶችን ነው፤

6) **“ወረዳ”** የሚለው በፈደራል ተቋማት ስር ያሉ ወረዳዎችን የሚያካትት **ነው።**

7) በዚህ መመሪያ በወንድ ጾታ የተገለፀው ለሴት ፆታም ያገለግላል፡፡

## ፫. የአደረጃጀትና መመሪያ መርሆዎች

፩) **አሳታፊነት**፡ መመሪያውን በውጤታማነት ለመተግበር በሁሉም የሊጉ አባላትና መዋቅሮች እንዲሁም የሁሉንም ባለድርሻ አካላት ተሳትፎና ቅንጅት በሚያረጋግጥ መልኩ ይከናወናል፤

፪) **ግልፀኝነት፡-** የአደረጃጀት ስራዎች በግልፀኝነት አሰራርን ተከትሎ የሚመራ ይሆናል።

፫) **ተጠያቂነት**፡ በየደረጃው ያሉ አስፈጻሚ አካላት የህግ የበላይነትን በማክበርና ለፓርቲ ዲስፕሊን ተገዢ በመሆን በተጠያቂነት መንፈስ መመሪያውን የሚያስፈጽሙ ይሆናል፡፡

፬) **ፍትሃዊነት**፡ መመሪያው ያለአድሎ፣ በመመሪያው የተቀመጡትን የአጠቃቀም መስፈርትን ብቻ መሰረት በማድረግ፣ የሁሉንም ክልሎችና መዋቅሮች ፍትሃዊ ተጠቃሚነት በሚያረጋግጥና የሊጉን ግቦች በሚያሳካ መንገድ ይፈጸማል፡፡

## ፬. የመመሪያው ዓላማ

የመመሪያው ዓላማ የብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ ተቋማዊ አደረጃጀቱን እና ተቋሙ በአሰራርና እንዲመራ ለማድረግ

## ፭. የመመሪያው ተፈፃሚነት ወሰን

ይህ አደረጃጀትና አሰራር መመሪያ የብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ መዋቅር ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል አንድ

### የዋና ጽ/ቤት እና የክልል ቅ/ጽ/ቤቶች ብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ አመራር አደረጃጀት፣ ተልዕኮና አሰራር

**አንቀጽ ፩፡-**

### የብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ ዋና ጽ/ቤት አመራር አደረጃጀት፣

የብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ መተዳደሪያ ደንብ እንደ ተጠበቀ ሆኖ የሊጉ ማዕከላዊ ኮሚቴና ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ውሳኔዎችን ለማስፈፀም የዋና ጽ/ቤት ወጣቶች ሊግ አመራር አካላት አደረጃጀት የሚከተሉት ይሆናሉ።

፩. የብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ ዋና ጽ/ቤት አስተባባሪ ኮሚቴ

፪. የብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ ዋና ጽ/ቤት አመራር ኮሚቴ

**አንቀጽ ፪፡**

### የብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ ዋና ጽ/ቤት አስተባባሪ ኮሚቴ

የብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ ዋና ጽ/ቤት አስተባባሪ ኮሚቴ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

፩. የብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ ፕሬዝዳንት ................................ ሰብሳቢ

፪. የብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ ምክትል ፕሬዝዳንቶች .................... አባል

፫. የብልፅግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ ጽ/ቤት ኃላፊ..............................አባል

፬. የብልፅግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ የፖለቲካ ዘርፍ ሃላፊ ..................... አባል

፭. የብልፅግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ የአደረጃጀት ዘርፍ ኃላፊ ............. አባል፣ የዋና ጽ/ቤቱ ወጣቶች ሊግ ጽ/ቤት አመራር ሆነው በስራ አሰፈፃሚ ኮሚቴው ውስጥ ያልተካተቱ ከሆነ በስራ አሰፈፃሚ ኮሚቴው መድረክ የሚሳተፉ ይሆናል።

**አንቀጽ ፫፡**

## የብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ ዋና ጽ/ቤት አስተባባሪ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት፣

1. በሊጉ ማዕከላዊ ኮሚቴና ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ውሳኔ መሰረት የሊጉን የፖለቲካ እና የድርጅት ስራዎች በበላይነት ያስተባብራሉ፣
2. የሊጉ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴና የማዕከላዊ ኮሚቴ ያወጣውን እቅድ አፈፃፀም ስራን ተከታትሎ ይፈፅማል፣ ያስፈፅማል፣
3. በፓርቲው እና በወጣቶች ሊግ የሚካሄዱ ስልጠናዎችን ያቅዳል፣ ይመራል ይከታተላል፣
4. በየደረጃው ያሉትን የሊጉን አመራር አካላትን ፖለቲካዊ ብቃት በመገንባት ተልዕኳቸውን የሚወጡ እንዲሆኑ የማብቃት ስራ ይሰራል፣
5. በሊጉ ማዕከላዊ ኮሚቴና ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የወጡ የአሰራርና የአደረጃጀት መመሪያዎች፣ የተቀመጡ አቅጣጫዎች በአግባቡ በስራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ እንዲፈፀም ድጋፍ ይሰጣል፣
6. ስለ ስራው ክንውን ለስራ አስፈፃሚ ኮሚቴዉ ሪፖርት ያቀርባል፣
7. የክልል አሰተባባሪ ኮሚቴወችን ከክልል የተላከለትን መነሻ ወሰዶ ይመድባል፤
8. የክልል ጽ/ቤቶች የአመራር ሹመት በክልሉ አስተባባሪ ኮሚቴዎች ታይቶ የተላከለትን አይቶ ያጸድቃል፡፡
9. ጠንካራ የክትትልና ድጋፍ ስርዓት በመዘርጋት ስራን ይመራል፣
10. ተጠሪነቱ ለሊጉ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ይሆናል፡፡

### አንቀጽ 4.

### የብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ ዋና ጽ/ቤት አስተባባሪ አመራር ኮሚቴ አሰራር

1. በየወሩ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፤ እንደ አስፈላጊነቱ ከዚህ ባጠረ ጊዜ ሊገናኝ ይችላል፡፡
2. ምልዓተ ጉባኤው 50+1 ነው፡፡
3. ውሳኔዎች በተባበረ ድምጽ የሚፀድቁ ሆኖ ድምፅ መስጠት አስፈላጊ ሲሆን በ50+1 የተደገፈ ሀሳብ በአካሉ ውሳኔ ሆኖ ይፀድቃል፡፡ እኩል ድምፅ ከመጣ ሰብሳቢው የደገፈው ሀሳብ የሚጸድቅ ይሆናል፡፡

### አንቀጽ 5፡

### የብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ ዋና ጽ/ቤት አመራር ኮሚቴ አደረጃጀት፣

የብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ ዋና ጽ/ቤት አመራር ኮሚቴ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡፡

1. የብልፅግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ ጽ/ቤት ኃላፊ ................................. ሰብሳቢ
2. የብልፅግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ ፖለቲካ ዘርፍ ኃላፊ .................. ም/ሰብሳቢ
3. የብልፅግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ አደረጃጀት ዘርፍ ኃላፊ ................... አባል፣

### አንቀጽ 6፡

### የብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ ዋና ጽ/ቤት አመራር ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት፣

፩. በሊጉ መተዳደሪያ ደንብ ላይ በተቀመጠው ተልዕኮ መሰረት የብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ የፖለቲካ፣ የአደረጃትና የህዝብ ግንኙነት ስራ ማዕከል ሆኖ ያገለግላል፡፡
፪. የወጣቶች ሊግ አመታዊ መነሻ እቅድ በማዘጋጀት በማዕከላዊ ኮሚቴው ሲፀድቅ ፈፃሚ አካላትን ለስራው ያዘጋጃል፡፡ ያሰማራል በስራው ሂደትም ተከታትሎ ይደግፋል፡፡ ስለአፈፃፀሙም ለወጣቶች ሊግ ፕሬዝዳንትና ለስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሪፖርት በማዘጋጀት ያቀርባል፣
፫. በፓርቲዉ እና በሊጉ የሚካሄደውን የአባላትና የአመራር የስልጠና ስራ ያጠናል፤ ያቅዳል፣ ያደራጃል፣ ስልጠናውንም እንዲካሄድ ያደርጋል፡፡
፬. የሊጉ የአሰራርና የአደረጃጀት መመሪያዎች፣ የማዕከላዊ ኮሚቴና የስራ አስፈፃሚ ውሳኔዎችና አቅጣጫዎች በስራ መተርጎማቸውን ይከታተላል ችግሮችን ይለያል፣ መፍትሄ አቅጣጫ ይቀይሳል፡
፭. የወጣቶች ሊግ ፕሮግራም፣ አቅጣጫዎች፣ የስራ አፈፃፀም እና ዕቅድ በሚዲያና በህዝብ ግንኙነት መሳሪያዎች ለህዝብ ያስተዋውቃሉ፡፡
፮. የሊጉ አባላት ማህደር መረጃ፣ የሊጉን በጀት፣ንብረትና ሰነዶች በበላይነት ያስተዳድራሉ፣ በጥንቃቄ እንዲያዙና በአግባቡ ስራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋሉ፣
፯. በስነምግባር የታነጸና የመፈጸም አቅም ያለው ጠንካራ የወጣት አመራርን በመፍጠር እና ለፓርቲዉ የወጣት አመራር መፍለቅያ ለመሆን በበቂ ቁጥር ለማብቃት ያቅዳል፣ ይፈፅማል፡፡
፰. የክልሉን ወጣቶች ሊግ መዋቅርን በቅርበት በመከታተል ተገቢውን ድጋፍ ይሰጣል፣
፱. የሊጉን የፋይናንስ ስራ ይከታተላል ይመራል ከዋና ፓርቲው ጽ/ቤት ጋር በቅንጅት የሊግ አባላቱን መዋጮ እና የተለያዩ ገቢዎችን ተከታትሎ ለአስተባባሪ ኮሚቴው ሪፖረት ያቀርባል፤
፲. የክትትልና የድጋፍ ሥራ ያከናውናል፣
፲፩. የሊጉ ልሳንና በራሪ ጽሁፎችን በመቅረጽ እና በፓርቲዉ ልሳን ውስጥ የወጣት ሊግ አምድ እንዲካተት በማድረግ የአባላት ፖለቲካ ግንባታ አጀንዳዎችን በመቅረፅ ያስተላልፋል፡፡
፲፪. የጽ/ቤቱን በጀት በማዘጋጀትና በፓርቲው ፋይናንስ ኮሚቴ በማቅረብ ሲጸድቅ በአግባቡ በስራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፡፡
፲፫. ተጠሪነቱ ለብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ ፕሬዚዳንት ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 7፡

### የብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ ዋና ጽ/ቤት አመራር ኮሚቴ አሰራር

፩. በየሳምንቱ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፣
፪. ምልዓተ ጉባዔው ፶0+፩ ነው፡፡
፫. ውሳኔዎች በተባበረ ድምፅ የሚፀድቁ ሆኖ ድምፅ መስጠት አስፈላጊ ሲሆን በ፶0+፩ የተደገፈ ሀሳብ የአካል ውሳኔ ሆኖ ይፀድቃል፡፡ እኩል ድምፅ ከመጣ ሰብሳቢው የደገፈው ሀሳብ የሚጸቅ ይሆናል፡፡

4. ሳምንታዊ አጭር የስራ ግምገማ ወርሃዊና በየሩብ አመቱ ለሚቀርቡ ሪፖርቶች ላይ በመመስረት ዘርዘር ያለ ግምገማ ያደርጋል፡፡
5. በየሩብ አመቱ ከክልል ወጣቶች ሊግ ጽ/ቤቶች ጋር መደበኛ ስብሰባ ያካሂዳል በየስድስት ወሩ ክልሎችን፣ ዞኖችንና ወረዳዎችን ናሙና በመውሰድ የታቀዱ ስራዎች እንዴት እየተከናወኑ እንዳሉ በአካል በመውረድ ያያል፣ ይገመግማል ድጋፍ ይሰጣል፡፡

## አንቀጽ 8.

## የክልል ብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ ቅ/ጽ/ቤት አመራር አደረጃጀት፣ ተልዕኮና አሠራር

የብልፅግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ መተዳደሪያ ደንብ እንደተጠበቀ ሆኖ የክልል ብልጽግናፓርቲ ወጣቶች ሊግ ቅ/ጽ/ቤት አመራር አካላት የሚከተሉት ይሆናሉ፡፡

1. የክልል ብልፅግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ ቅ/ጽ/ቤት አስተባባሪ ኮሚቴ
2. የክልል ብልፅግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ ቅ/ጽ/ቤት አመራር ኮሚቴ

## አንቀጽ 9.

## የክልል ብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ ቅ/ጽ/ቤት አስተባባሪ ኮሚቴ አደረጃጀት

የክልል አስተባባሪ ኮሚቴ 9 አባላት ያሉት ሲሆን በሊጉ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የሚመደቡ ሆነው ከመካከላቸው ሰብሳቢና ምክትል ሰብሳቢ ይመርጣሉ፡፡ የክልሉ ወጣቶች ሊግ ጽ/ቤት አመራር አባላት በአስተባባሪ ኮሚቴው ውስጥ ያልተካተቱ ከሆኑ በአስተባባሪ ኮሚቴው መድረክ የሚሳተፉ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 10.

የክልል ብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ አስተባባሪ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

1. የዞን አሰተባባሪ ኮሚቴዎችን ያደራጃል/ይመድባል፤
2. ከወጣቶች ሊግ ብልጽግና ፓርቲ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በሚሰጠው አቅጣጫ መሰረት የወጣቶች ሊግ የፖለቲካ እና የድርጅት ሥራዎች በበላይነት ያስተባብራሉ፣
3. የሊጉ አስተባባሪ ኮሚቴ ዕቅድ አፈፃፀም ስራን ተከታትሎ ይፈፅማል፣ ያስፈፅማል፣
4. የብልፅግና ፓርቲንና የሊጉን እንዲሁም በመንግስት ስራዎችን ውስጥ የወጣቱ ተጠቃሚነት እና ተሳታፊነት እንዲረጋገጥ ተግባራት ተቀናጅተው እንዲተገበሩ ያደርጋል፣
5. በክልሉ የሚካሄዱ የፓርቲና የሊግ ስልጠናዎችን ወጣቶችን ያሳተፈ እንዲሆን ያቅዳል፣ ይመራል ይከታተላል፣
6. የክልሉን ብልጽግና ወጣቶች የመፈጸም ብቃት በማዳበር በስነምግባር የታነጸና የመፈጸም አቅም ያለው

ጠንካራ የወጣት አመራርን በመፍጠር እና ለፓርቲዉ የወጣት አመራር መፍለቅያ እንድመሆን ያቅዳል፣ ይፈፅማል፡፡

7. በብልጽግና ወጣቶች ሊግ ማዕከላዊ ኮሚቴና ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የወጡ የአሰራርና የአደረጃጀት መመሪያዎች፣ የተቀመጡ አቅጣጫዎችን በአግባቡ በስራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ እንዲፈፀም ድጋፍ ይሰጣል፣

8. የክልል የብልጽግና ወጣቶች ሊግ አመራር እና በተዋረድ በሚሰጡ የብልጽግና ወጣቶች ሊግ ሹመት ለፓርቲ ጽ/ቤት ያቀርባል፣ ሲጸድቅ ያሰማራል፣

9. የሊጉን የፋይናንስ ስራዎች ከፓርቲዉ የፋይናንስ አካላት ጋር በመቀናጀት የሊጉን የአባላት መዋጮ ይከታተላል፤ የደረሰበትን ይገመግማል፣

10. ስለ አጠቃላይ የወጣት ሊግ ሥራ አፈጻጸም ለሊጉ ኮንፈረንሱ ሪፖርት ያቀርባል፡፡

11. ጠንካራ የክትትልና ድጋፍ ስርአት በመዘርጋት ስራን ይመራል፣

12. ተጠሪነቱ ለሊጉ ስራ አስፈጻሚ እና ለብልጽግና ወጣቶች ሊግ ዋና ጽ/ቤት ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 11.**

የክልል ብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ ቅ/ጽ/ቤት አስተባባሪ ኮሚቴ አሰራር

1. በሶስት ወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፡፡ እንደ አስፈላጊነቱ ከዚህ ባነሰ ጊዜ ሊገናኝ ይችላል፡፡
2. ምልዓተ ጉባዔው 50+1 ነው፡፡
3. ውሳኔዎች በተባበረ ድምጽ የሚፀድቁ ሆኖ ድምፅ መስጠት አስፈላጊ ሲሆን በ50+1 የተደገፈ ሀሳብ የአካሉ ውሳኔ ሆኖ ይፀድቃል፡፡ እኩል ድምፅ ከመጣ ሰብሳቢው የደገፈው ሀሳብ ፀዳቂ ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 12.**

የክልል ብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ ቅ/ጽ/ቤት አመራር ኮሚቴ አደረጃጀት

የክልል ብልፅግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ ቅ/ጽ/ቤት አመራር ኮሚቴ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል

**ለኦሮሚያ፡አማራና አዲስ አባባ**

1. የክልል ብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ ቅ/ጽ/ቤት ኃላፊ ………………… ሰብሳቢ

፪. የክልል ብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ ፖለቲካ ዘርፍ ኃላፊ ............ ም/ሰብሳቢ

፫. የብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ አደረጃጀት ዘርፍ ኃላፊ ..................... አባል

**ለሌሎች ክልሎችና ከተማ አስተዳደር**

፩. የክልል ብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ ቅ/ጽ/ቤት ኃላፊ ..................... ሰብሳቢ

፪. የክልል ብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ የፖለቲካና አደረጃጀት ዘርፍ ኃላፊ..አባል

## አንቀጽ ፲፫.

### የክልል ብልፅግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ ቅ/ጽ/ቤት አመራር ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

፩. በሊጉ መተዳደሪያ ደንብ ላይ በተቀመጠው ተልዕኮ መሰረት የክልሉ ብልጽግና ወጣቶች ሊግ የፖለቲካዊ፣ የአደረጃጀትና የሕዝብ ግንኙነት ስራ ማዕከል ሆኖ ያገለግላል።

፪. ከብልጽግና ፓርቲ ዋና ጽ/ቤት የሚወርዱ ዕቅዶችን መነሻ በማድረግ ከራሱ ክልል ወጣቶች ሁኔታ ጋር በማጣጣም የፖለቲካና የአደረጃጀት ስራዎችን ያቅዳል፣ ፈፃሚ አካላትን ለስራው ያዘጋጃል፣ ያሰማራል በስራው ሂደትም ተከታትሎ ይደግፋል።

፫. የአባላት የዕለት ተዕለት ግንባታ ስራን በተቀመጠው አቅጣጫ እየተከናወነ መሆኑንና በየወቅቱ ያለውን የአባላት ፖለቲካዊ ሁኔታ በመገምገም የግንባታ ስራው እያጠናከረ ይሄዳል። ጠንካራ የብልጽግና ወጣቶች ሊግ ሕዋስና መሰረታዊ ድርጅት አመራር የመፍጠር ስራን ያቅዳል ተግባራዊ መሆኑንም ያረጋግጣል።

፬. በፓርቲው የሚካሄደውን የአባላትና የአመራር ስልጠና የወጣቶችን ተሳትፎ በቂ መሆኑን እና በአጠቃላይ የስልጠናውን ሁኔታ ይከታተላል፤ የሊጉን ስልጠናዎች ያቅዳል፣ ያደራጃል ስልጠናውም እንዲካሄድ ያደርጋል።

፭. የብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ የአሰራርና የአደረጃጀት መመሪያዎች፣ የማዕከላዊ ኮሚቴና የስራ አስፈፃሚ ውሳኔዎችና አቅጣጫዎች በስራ መተርጎማቸውን ይከታተላል ችግሮችን ይለያል፣ የመፍትሔ አቅጣጫ ይቀይሳል።

፮. በብልጽግና ወጣቶች ሊግ ዋና ጽ/ቤት በሚሰጠው አቅጣጫ መሰረት የሊጉ ፕሮግራም፣ አቅጣጫዎች፣ የሥራ ዕቅዶች እና አፈፃፀም በሚዲያና በሕዝብ ግንኙነት መሳሪያዎች ለሕዝብ ያስተዋውቃል፤

፯. በክልሉ የሚገኙ የብልጽግና ወጣቶች ሊግ አባላት ማህደር መረጃ፣ የሊጉን በጀት፣ ንብረትና ሰነዶች በበላይነት ያስተዳድራሉ፣ በጥንቃቄ እንዲያዙና በአግባቡ ሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋሉ፣

፰. በስነምግባር የታነፀና የመፈጸም አቅም ያለው ጠንካራ የወጣት አመራርን በመፍጠር እና ለፓርቲዉ የወጣት አመራር መፍለቅያ ለመሆን በበቂ ቁጥር ለማብቃት ያቅዳል፣ ይፈፅማል።

፱. የዞን የከተማና የወረዳ የብልጽግና ወጣቶች ሊግ አመራርን በቅርበት በመከታተል ተገቢውን ድጋፍ ይሰጣል፤

10. የሊጉን የፋይናንስ ስራዎች ከፓርቲው የፋይናንስ ዘርፍ ጋር በመቀናጀት ይከታተላል ይደግፋል የአባላቱን መዋጮ እና አጠቃላይ የሊጉን ገቢ ሪፖርት ያቀርባል፡፡
11. የክትትልና ድጋፍ ሥራ ያከናውናል፡፡
12. ለብልጽግና ወጣቶች ሊግ ልሳንና በራሪ ጽሑፎች ለሚካሄደው የአባላት ግንባታ አጀንዳዎችን በመቅረጽ ያስተላልፋል፡፡
13. የጽ/ቤቱን በጀት በአግባቡ በስራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፣
14. ተጠሪነቱ ለክልሉ ብልጽግና ወጣቶች ሊግ አስተባባሪ ኮሚቴና ለብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ ዋና ጽ/ቤት ይሆናል፡፡

### አንቀጽ 14፡

የክልል ብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ ቅ/ጽ/ቤት አመራር ኮሚቴ አሰራር፣

1. በየሁለት ሳምንቱ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፣
2. ምልዓተ ጉባኤው 50+1 ነው፡፡
3. ውሳኔዎች በተባበረ ድምጽ የሚፀድቁ ሆኖ ድምፅ መስጠት አስፈላጊ ሲሆን በ50+1 የተደገፈ ሀሳብ የአካሉ ውሳኔ ሆኖ ይፀድቃል፡፡ እኩል ድምፅ ከመጣ ሰብሳቢው የደገፈው ሀሳብ ፀዳቂ ይሆናል፡፡
4. ሳምንታዊ አጭር የስራ ግምገማ፣ ወርሃዊና በየሩብ አመቱ ለሚቀርቡ ሪፖርቶች ላይ በመመስረት ዘርዘር ያለ ግምገማ ይደረጋል፡፡
5. በየሶስት ወር በክልሉ ካሉት ዞኖችና ለክልል ተጠሪ የሆኑ ከተሞችን በየ6 ወሩ ወረዳዎችን ናሙና በመውሰድ የታቀዱ ስራዎች እንዴት እየተከናወኑ እንዳሉ በአካል በመውረድ ያያል፣ ይገመግማል ድጋፍ ይሰጣል፡፡
6. ለብልፅግና ፓርቲ ዋና ጽ/ቤት በ2 ሳምንት የስራ ኢንፎርሜሽን ልውውጥ ያደርጋል፣ በወር አጭር የፅሑፍ ሪፖርት፣ በየ3 ወሩ አጠቃላይ የስራ ሪፖርትና የጋራ መድረክ ይኖረዋል፡፡

## ክፍል ሁለት

### የዞን/የልዩ ወረዳ ወጣቶች ሊግ ቅ/ጽ/ቤት አመራር አደረጃጀት፣ተልዕኮና አሰራር

### አንቀጽ 15፡

የዞን/የልዩ ወረዳ ወጣቶች ሊግ ቅ/ጽ/ቤት አመራር አካላት አደረጃጀት

የብልፅግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ መተዳደሪያ ደንብ እንደተጠበቀ ሆኖ የዞን/የልዩ ወረዳ ወጣቶች ሊግ አመራር አካላት የሚከተሉት ይሆናሉ፡፡

1. የዞን/የልዩ ወረዳ ብልፅግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ አስተባባሪ ኮሚቴ
2. የዞን/የልዩ ወረዳ ብልፅግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ ቅ/ጽ/ቤት አመራር

## አንቀጽ 16.

### የዞን/የልዩ ወረዳ ብልጽግና ወጣቶች ሊግ አስተባባሪ ኮሚቴ አደረጃጀት

የዞን/የልዩ ወረዳ አስተባባሪ ኮሚቴ የዞን/የልዩ ወረዳ የብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ 7 አባላት ያሉት ሆኖ በክልል አስተባባሪ የሚመደቡ ከመካከላቸው ሰብሳቢና ምክትል ሰብሳቢ ይመርጣሉ፡፡ የዞን/የልዩ ወረዳ ብልጽግና ወጣቶች ሊግ ጽ/ቤት የአመራር አባላት በምደባ ካልተካተቱ በአስተባባሪ መድረኩ የሚሳተፉ ይሆናሉ፡፡

## አንቀጽ 17.

### የዞን/የልዩ ወረዳ ብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ አስተባባሪ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

1. ከክልሉ ብልጽግና ወጣቶች ሊግ አሰተተባባሪ ኮሚቴ በሚሰጠው አቅጣጫ መሰረት የወጣቶች ሊግ የፖለቲካ እና የአደረጃጀት ሥራዎችን የእለት ተእለት እንቅስቃሴ በበላይነት ይመራል፤
2. የሊጉን ዕቅድ አፈፃፀም ስራን ተከታትሎ ይፈፅማል፣ ያስፈፅማል፣
3. የብልፅግና ፓርቲንና የሊጉን እንዲሁም በመንግስት ስራዎችን ውስጥ የወጣቶችን ተጠቃሚነት እና ተሳታፊነት እንዲረጋገጥ ተግባራት ተቀናጅተው እንዲተገበሩ ያደርጋል፣
4. የዞን/የልዩ ወረዳ የሚካሄዱ የፓርቲና የሊግ ስልጠናዎች ወጣቶችን ያሳተፋል እንዲሁም ያቅዳል፣ ይመራል ይከታተላል፣
5. የወጣት አመራር የመፈፀም ብቃትን በማዳበር የወጣት አባላትን የተደራጀ እንቅስቃሴ የሚመራ ጠንካራ የወጣት አመራርን በመፍጠር እና ለፓርቲዉ የወጣት አመራር መፍለቅያ በመሆን በበቂ ቁጥር ለማብቃት ያቅዳል፣ ይፈፅማል፡
6. በክልሉ ብልፅግና ወጣቶች ሊግ አስተባባሪ ኮሚቴ የወጡ የአሰራርና የአደረጃጀት መመሪያዎች፣ የተቀመጡ አቅጣጫዎች በአግባቡ በስራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ እንዲፈፀም ድጋፍ ይሰጣል፣
7. የዞን/የልዩ ወረዳ የብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ ቅ/ፅ/ቤት አመራር እና በተዋረድ በሚሰጡ የወጣቶች ሊግ ሹመት ለፓርቲ ጽ/ቤት ያቀርባል፣ ሲጸድቅ ያሰማራል፣
8. የዞኑን/የከተማዉን የሊግ አባላቱን ገቢዎች ይከታተላል ሪፖርቱን ይገመግማል አቅጣጫ ይሰጣል፡፡

፱. ስለ ሥራው ክንውን ለሊግ ለኮንፈረንስ እና ለክልሉ ብልጽግና ወጣቶች ሊግ ጽ/ቤት ሪፖርት ያቀርባል፡፡

፲. ጠንካራ የክትትልና ድጋፍ ስርአት በመዘርጋት ስራን ይመራል፣

፲፩. ተጠሪነቱ ለዞኑ ብልፅግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ ኮንፈረንስና ለክልሉ ሊግ አስተባባሪ ይሆናል፡፡

**አንቀጽ ፲፰.**

## የዞን/የልዩ ወረዳ ብልፅግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ አስተባባሪ ኮሚቴ አሰራር

፩. ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ይኖራቸዋል፡፡ አስቸካይ እና አሰፈላጊ ሲሆን ከዚህ ባጠረ ጊዜ ሊገናኙ ይችላሉ ፡፡

፪. ምልዓተ ጉባዔው ፶0+፩ ነው፡፡

፫. ውሳኔዎች በተባበረ ድምጽ የሚፀድቁ ሆኖ ድምፅ መስጠት አስፈላጊ ሲሆን በ፶0+፩ የተደገፈ ሀሳብ የአካሉ ውሳኔ ሆኖ ይፀድቃል፡፡ እኩል ድምፅ ከመጣ ሰብሳቢው የደገፈው ሀሳብ ፀዳቂ ይሆናል፡፡

**አንቀጽ ፲፱.**

**የዞን/የልዩ ወረዳ ብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ ቅ/ጽ/ቤት አመራር አደረጃጀት** የዞን/የልዩ ወረዳ ብልፅግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ ቅ/ጽ/ቤት አመራር የሚከተለው ይኖሩታል

፩ የዞን/የልዩ ወረዳ ብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ ቅ/ጽ/ቤት ኃላፊ

**አንቀጽ ፳0.**

የዞን/የልዩ ወረዳ ብልፅግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ ቅ/ጽ/ቤት አመራር ተግባርና ኃላፊነት

፩. በሊጉ መተዳደሪያ ደንብ ላይ በተቀመጠው ተልዕኮ መሰረት የዞን/የልዩ ወረዳ ብልጽግና ወጣቶች ሊግ የፖለቲካዊ፣ የአደረጃጀትና የሕዝብ ግንኙነት ስራ ማዕከል ሆኖ ያገለግላል፡፡

፪. ከክልል ብልጽግና ወጣቶች ሊግ ቅ/ጽ/ቤት የሚወርዱ ዕቅዶችን መነሻ በማድረግ የዞን/የልዩ ወረዳ ወጣቶች ሁኔታ ጋር በማጣጣም የፖለቲካና የአደረጃጀት ስራዎችን ያቅዳል፣ ፈፃሚ አካላትን ለስራው ያዘጋጃል፣ ያሰማራል በስራው ሂደትም ተከታትሎ ይደግፋል፡፡

፫. የአባላት የዕለት ተዕለት ግንባታ ስራን በተቀመጠው አቅጣጫ እየተከናወነ መሆኑንና በየወቅቱ ያለውን የአባላት ፖለቲካዊ ሁኔታ በመገምገም የግንባታ ስራው እያጠናከረ ይሄዳል፡፡ ጠንካራ የወጣቶች ሊግ ሕዋስና መሰረታዊ ድርጅት አመራር የመፍጠር ስራን ያቅዳል ተግባራዊ መሆኑንም ያረጋግጣል፡፡

፬. በፓርቲው በሚካሄደውን የአባላትና የአመራር ስልጠና የወጣቶችን ተሳትፎ ምጥጥን መሆኑን እና በአጠቃላይ የስልጠናውን ሁኔታ ይከታተላል፤ የሊጉን ስልጠና ያቅዳል፣ ያደራጃል በስልጠናው ወጣቶች እንዲሳተፉ ያደርጋል፡፡

፭. የብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ የአሰራርና የአደረጃጀት መመሪያዎች፣ የማዕከላዊ ኮሚቴና የስራ አስፈፃሚ ውሳኔዎችና አቅጣጫዎች በስራ መተርጎማቸውን ይከታተላል፤ ችግሮችን ይለያል፤ የመፍትሔ

አቅጣጫ ይቀይሳል፡፡

6. በብልጽግና ወጣቶች ሊግ እና በፓርቲው ጽ/ቤት በሚሰጠው አቅጣጫ መሰረት የሊጉ ፕሮግራም፣ አቅጣጫዎች፣ የሥራ አፈፃፀም እና ዕቅዶች በሚዲያና በሕዝብ ግንኙነት መሳሪያዎች ለሕዝብ ያስተዋውቃሉ፣
7. የዞን/የልዩ ወረዳ የሚገኙ የብልጽግና ወጣቶች ሊግ አባላት ማህደር መረጃ፣ የሊጉን በጀት፣ ንብረትና ሰነዶች በበላይነት ያስተዳድራሉ፣ በጥንቃቄ እንዲያዙና በአግባቡ ሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋሉ፣
8. በስነምግባር የታነጸችና የመፈጸም አቅም ያላት ጠንካራ የወጣት አመራርን በመፍጠር እና ለፓርቲዉ የወጣት አመራር መፍለቅያ ለመሆን በበቂ ቁጥር ለማብቃት ያቅዳል፣ ይፈፅማል፡፡
9. የከተማና የወረዳ የብልጽግና ወጣቶች ሊግ አመራርን በቅርበት በመከታተል ተገቢውን ድጋፍ መስጠት፡፡
10. የሊጉን ገቢዎች ይከታተላል፡ ያስፈጽማል ከዞኑ ብልጽግና ፓርቲ ጸ/ቤት ጋር በቅንጅት ገምግሞ ሪፖርት ያቀርባል፡፡
11. የሚከተለውን የክትትልና ድጋፍ ሥራ ያከናውናል፡-
    1. በ2 ሳምንት የስራ ኢንፎርሜሽን ልውውጥ ያደርጋል፣
    2. በወር አጭር የፅሑፍ ሪፖርት፣
    3. በየስድስት (6) ወሩ አጠቃላይ የስራ ሪፖርትና የጋራ መድረክ ይኖረዋል፡፡ ለዚህም ምዘና ተደርጎ ኦርኔል ይሞላል፡፡
12. በብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ ልሳንና በራሪ ጽሑፎች የሚተላለፉትን መልህክቶች ከዞኑ እና ከከተማ አሰተዳደሩ ጋር አጣትሞ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡
13. ተጠሪነቱ ለክልሉ ወጣቶች ሊግ አስተባባሪ ኮሚቴ ለክልሉ ብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ ጽ/ቤት ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 21.

### የዞን/የልዩ ወረዳ ብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ ቅ/ጽ/ቤት አመራር አሰራር፣

1. የወረዳ/የከተማ/ቀበሌ ወጣቶች ሊግ አመራርን በቅርበት በመከታተል ተገቢውን ድጋፍ መስጠት፡፡

ሀ) በየሩብ አመቱ ከወዳ/ከተማ/ቀበሌ ቅ/ጽ/ቤት ወጣቶች ሊግ አመራር ጋር የስራ ግምገማ ያደርጋል፡፡

ለ) በየወሩ ወረዳዎች/ቀበሌዎች ያሉበት የአፈፃፀም ደረጃ የጽሁፍ ሪፖርት ተቀብሎ ተገቢውን ግብረ መልስና ድጋፍ ይሰጣል፡፡

ሐ) በየሳምንቱ ከወረዳዎች/ቀበሌዎች ጋር በስልክ የመረጃ ልውውጥ በማድረግ ኢንፎርሜሽን ይቀበላል፡፡

መ) አመታዊ የስራ አፈፃፀም ግምገማና የቀጣይ አመት እቅድ ለወረዳ/ከተማ/ቀበሌ ለሊግ አመራር ኦረንቴሽን ይሰጣል፡፡ በየ3 ወሩ ደግሞ ከጠንካራ፣ መካከለኛና ደካማ ወረዳዎች/ቀበሌዎች ናሙና በመውሰድ የታቀዱ ስራዎች እንዴት እየተከናወኑ እንዳሉ በአካል ይገመግል የድጋፍ አቅጣጫንም

ያስቀምጣል፡፡

# ክፍል ሶስት

## አንቀጽ ፳፪.

### የወረዳ ብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ አመራር አደረጃጀት፣ ተልዕኮና አሰራር

የወረዳ ብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ አመራር አካላት አደረጃጀት፣ የወረዳ ወጣቶች ሊግ አመራር አካላት የሚከተሉት ይሆናሉ፡፡

1. የወጣቶች ሊግ አስተባባሪ ኮሚቴ፣
2. የወጣቶች ሊግ ጽ/ቤት አመራር

## አንቀፅ ፳፫.

### የወረዳ ብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ አስተባባሪ ኮሚቴ አደረጃጀት፣

የወረዳ ብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ አስተባባሪ ኮሚቴ በዞን አስተባባሪ ኮሚቴ የሚመደቡ 7 አባላትን የሚኖሩት ሆኖ ከመሀከላቸው ሰብሳቢና ምክትል ሰብሳቢ ይመርጣሉ፡፡ የወረዳው ወጣቶች ሊግ ጽ/ቤት አመራሮች በአስተባባሪነት ባየመደቡ በአስተባባሪ ኮሚቴው መድረክ የሚሳተፉ ይሆናሉ፡፡

## አንቀጽ ፳፬.

### የወረዳ ብልፅግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ አስተባባሪ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

1. ከዞን ብልጽግና ወጣቶች ሊግ አስተባባሪ ኮሚቴ በሚሰጠው አቅጣጫ መሰረት የወረዳውን የብልጽግና ወጣቶች ሊግ  የፖለቲካ ስራና የመንግስት ስራዎችን የእለት ተእለት እንቅስቃሴ ይከታተላል፤ ይመራል፣
2. በወረዳው የሚካሄዱ የብልጽግና ወጣቶች ሊግ፣ የፓርቲና የመንግስት የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን ይከታተላል፣ በሂደቱም የወጣቶችን ተሳትፎ መሟላቱን ያረጋግጣል፤ የቀበሌ የወጣቶች ሊግ አመራር አካላትን በቅርብ ይደግፋል፡፡
3. የብልጽግና ወጣቶች ሊግ አባላት እና የወጣት አመራር አካላትን ፖለቲካዊ ብቃት በመገንባት ተልዕኳቸውን የሚወጡ እንዲሆኑ ጠንካራ ስራ ይሰራል፡፡
4. የብልጽግና ወጣቶች ሊግ አመራር ምደባ የውሳኔ ሀሳብ በወረዳዉ ላለው የፓርቲ ጽ/ቤት ያቀርባሉ፣ ሲጸድቅ ያሰማራሉ፣
5. ከሊጉ ማዕከላዊ ኮሚቴና ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የወጡ የአሰራርና የአደረጃጀት መመሪያዎች፣ የተቀመጡ አቅጣጫዎች በአግባቡ በስራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፤ ያስፈፅማል፣ ይፈፅማል፡፡
6. ተጠሪነቱ ለዞን አስተባባሪ ኮሚቴ እና ለዞኑ ወጣቶች ሊግ ጽ/ቤት ይሆናል፡፡

**አንቀጽ ፳፭.**

የወረዳ ብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ አስተባባሪ ኮሚቴ አሰራር

1. በወር አንዴ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፡፡ በወሩ ውስጥ ትኩረት የሚሰጣቸው ጉዳዮች ላይ አቅጣጫ ያስቀምጣል፡፡
2. ምልዓተ ጉባኤው 50+1 ነው፡፡
3. ውሳኔዎች በተባበረ ድምጽ የሚፀድቁ ሆኖ ድምፅ መስጠት አስፈላጊ ሲሆን በ50+1 የተደገፈ ሀሳብ የአካሉ ውሳኔ ሆኖ ይፀድቃል፡፡ እኩል ድምፅ ከመጣ ሰብሳቢው የደገፈው ሀሳብ ፀዳቂ ይሆናል፡፡

**አንቀጽ ፳፮.**

የወረዳ ብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ ጽ/ቤት አመራር አደረጃጀት፣

የወረዳ ወጣቶች ሊግ ጽ/ቤት ስራ አመራር የሚከተለው ይሆናሉ፡፡

1. የወረዳ ብልፅግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ ጽ/ቤት ኃላፊ

**አንቀጽ ፳፯.**

የወረዳው ብልጽግና ፓርቲ የወጣቶች ሊጉ ጽ/ቤት ስራ አመራር ተግባርና ኃላፊነት

1. የሊጉ ጽ/ቤት በመተዳደሪያ ደንብ ላይ በተቀመጠው ተልዕኮ መሰረት የወረዳ የፖለቲካ፣ የአደረጃጀትና የህዝብ ግንኙነት ስራ ማዕከል ሆኖ ያገለግላል፡፡
2. ከዞን ብልጽግና ወጣቶች ሊግ ጽ/ቤት የሚወርዱ እቅዶችን መነሻ በማድረግ ከራሱ ሁኔታ ጋር በማጣጣም የፖለቲካና የአደረጃጀት ስራዎችን ያቅዳል፣ ፈፃሚውን አካል ኦረንቴሽን ሰጥቶ ያሰማራል፣ የስራውን አፈፃፀም ይከታተላል፣ ይመራል፣
3. የሊግ አደረጃጀት አመራርና አባላት በስራቸው ግምባር ቀደም እንዲሆኑ ፖለቲካዊ ግንዛቤያቸው እንዲዳብር ያደርጋል፣
4. በወረዳው የሊግ አባላት የሚካሄደውን የልማት፣ የመልካም አስተዳደር፣ የፖለቲካዊና አደረጃጀት ስራዎች ከመተግበር አኳያ ያሉ መልካም ልምዶችን ይቀምራል እንዲስፋፉ ያደርጋል፡
5. የአባላት የእለት ተእለት ግንባታ ስራን በተቀመጠው አቅጣጫ እየተከናወነ መሆኑንና በየወቅቱ ያለውን የወጣቶች ሊግ አባላት ፖለቲካዊ ሁኔታ በመገምገም የግንባታ ስራው እያጠናከረ ይሄዳል፡፡ ጠንካራ የሊግ የህዋስና መሰረታዊ ድርጅት አመራር የመፍጠር ስራን ያቅዳል፣ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፣ ይመራል፣
6. በወረዳ የሚካሄደውን የአባላትና የአመራር ስልጠና፣ ሴሚናር፣ የመ/ድርጅቶች ኮንፈረንስ ያስተባብራል፣

ይመራል፣

7. የሊጉ የአሰራርና የአደረጃጀት መመሪያዎች፣ የማዕከላዊ ኮሚቴና የስራ አስፈፃሚ ውሳኔዎችና አቅጣጫዎች በስራ መተርጎማቸውን ይከታተላል ያስፈፅማል፣ ይፈጽማል፣
8. በወረዳ ውስጥ በሚገኙ ሊጉ የአባላት ማህደር መረጃ የሊጉ ሰነዶች ገንዘብና ንብረት በበላይነት ያስተዳድራል፣ በጥንቃቄ እንዲያዙና በአግባቡ ስራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፣
9. በስነምግባር የታነጸና የመፈጸም አቅም ያለው ጠንካራ የወጣት አመራርን በመፍጠር እና ለፓርቲዉ የወጣት አመራር መፍለቅያ ለመሆን በበቂ ቁጥር ለማብቃት ያቅዳል፣ ይፈፅማል፡፡
10. በልሳናትና በራሪ ጽሁፎች እንዲሁም በብልጽግና መጽሄት ላይ ለሚካሄደው የአባላት ግንባታ ከዞን ፓርቲ ጽ/ቤት የሚተላለፉትን ከወረዳ ሁኔታ ጋር አጣጥሞ ተግባራዊ ያደርጋል፣
11. የሊጉን የገቢ ሰርዓት ይመራል ይከታተላል ሥለ አባላቱ መዋጮ ከፓርቲዉ ፋይናንስ ክፍል ጋር በቅንጅት ሪፖርት አቅርቦ ይገመግማል
12. ተጠሪነቱ ለዞን አስተባባሪ ኮሚቴና ለዞን/ለከተማ አስተዳደር ወጣቶች ሊግ ጽ/ቤት አመራር ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 28.**

የወረዳ ብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ ጽ/ቤት አመራር አሰራር

1. የቀበሌ ብልጽግና ወጣቶች ሊግ አመራርን በቅርበት በመከታተል ተገቢውን ድጋፍ መስጠት፡፡
   ሀ) በየሩብ አመቱ ከቀበሌ ጽ/ቤት ወጣቶች ሊግ አመራር ጋር የስራ ግምገማ ያደርጋል፡፡
   ለ) በየወሩ ቀበሌዎች ያሉበት የአፈፃፀም ደረጃ የጽሁፍ ሪፖርት ተቀብሎ ተገቢውን ግብረ መልስና ድጋፍ ይሰጣል፡፡
   ሐ) በየሳምንቱ ከቀበሌዎች ጋር በስልክ የመረጃ ልውውጥ በማድረግ ኢንፎርሜሽን ይቀበላል፡፡
   መ) አመታዊ የስራ አፈፃፀም ግምገማና የቀጣይ አመት እቅድ ለቀበሌ ለሊግ አመራር ኦረንቴሽን ይሰጣል፡፡ በየ3 ወሩ ደግሞ ከጠንካራ፣ መካከለኛና ደካማ ቀበሌዎች ናሙና በመውሰድ የታቀዱ ስራዎች እንዴት እየተከናወኑ እንዳሉ በአካል ይገመግል የድጋፍ አቅጣጫንም ያስቀምጣል፡፡

## ክፍል አራት

የአዲስ አበባ፣ ድሬዳዋ፤ ለክልል ተጠሪ የሆኑ ከተሞች ፤**የፌደራል ተቋማት እና ሴክተር ማስራቤቶች** የብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ አመራር አደረጃጀት፣ ተልዕኮና አሰራር

**አንቀጽ 29፡**

የብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ አመራር አካላት **የከተማ/አስተዳደሩ**

የብልጽግና ፓርቲ የወጣቶች ሊግ አመራር አካላት የሚከተሉት ናቸው።

1. የከተማ አስተዳደሩ የብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ አስተባባሪ ኮሚቴ፣
2. የከተማ አስተዳደሩ የብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ ጽ/ቤት አመራር ኮሚቴ

**አንቀጽ 30፡**

የከተማ አስተዳደሩ የብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ አስተባባሪ ኮሚቴ አደረጃጀት

የከተማ የአስተዳደሩ የወጣቶች ሊግ አስተባባሪ ኮሚቴ በሊጉ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የሚመደቡ/ የሚወከሉ 9 አባላት ያሉት ሆኖ ከመካከላቸው ሰብሳቢና ምክትል ሰብሳቢ ይመርጣሉ። የከተማዉ ወጣቶች ወጣቶች ሊግ ጽ/ቤት አመራር በአስተባባሪነት ባይመደቡ እንኳን በአስተባባሪ ኮሚቴው መድረክ ተሳታፊዎች ይሆናሉ።

**አንቀጽ 31.**

የከተማ አስተዳደሩ የብልጽግና ፓርቲ የወጣቶች ሊግ አስተባባሪ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

1. ከብልጽግና ወጣቶች ሊግ ዋና ጽ/ቤት አስተባባሪ ኮሚቴ እና ከሊጉ ዋና ጽ/ቤት በሚሰጠው አቅጣጫ መሰረት የከተማውን የወጣቶች የፖለቲካ ስራና የመንግስት ስራዎች በወጣቶች ዙሪያ ያለዉን የእለት ከእለት እንቅስቃሴ ይከታተላል ይመራል፣
2. የከተማ/አስተዳደሩ የብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ ቅ/ጽ/ቤት እንዲሁም የሊጉ አሰተባባሪ ኮሚቴ አጠቃላይ የአመራር ውሳኔዎችና አቅጣጫዎች በተሟላ መንገድ በስራ ላይ እንዲውሉ መከታተል፣ ማስፈፀም፣ መፈፀም ፤
3. በከተማ አስተዳደሩ የሚገኙ የወጣት አደረጃጀቶች እና መሰረታዊ ድርጅትና የህዋስ አመራር በስሩ ያሉትን አባላት አደራጅቶ ለማንቀሳቀስ የሚያስችል አቅም እንዲኖረው ማስቻል፣ የአደረጃጀቶችን ጥሩ ልምድ እና ተሞክሮ ቀምሮ እንዲሰፋ ያደርጋል።
4. የከተማ አስተዳደሩን የብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ መሰረታዊ ድርጅትና የህዋስ አመራር አካላት በሊጉ አደረጃጀትና የአሰራር መመሪያዎች ላይ በቂ ግንዛቤ ይዞ በስራ ላይ እንዲውል ያደርጋል።
5. በከተማው አስተዳደሩ በሚካሄዱ ኢንቨስትመንት፣ ለመካከለኛና አነስተኛ የማምረትና አገልግሎት ሰጭ ተቋማት መስፋፋት ምቹ ሁኔታ ከሚፈጥሩ አካላት ጋር የወጣቶች ተሳትፎ እና ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ፤ የስራ እድልን ማስፋት፣ የወጣቶች መልካም አስተዳደር ችግርን መለየት፣ የከተማው የመኖሪያ ቤት እጥረት እንዲቀረፍ ሲሰራ እና በከተማው የቤት መስሪያ ቦታም ሆነ መስሪያና መሸጫ መሬት ወይ ሼድ ሲሰጥ ወጣቶች ታሳቢ ባደረገ መልኩ መፈጸሙን መከታተልና ተፈጻሚ እንዲሆን መስራት።
6. የአዲስ አበባና የድሬዳዋ ብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ አስተባባሪ ኮሚቴ ተጠሪነታቸው ለብልጽግና ወጣቶች ሊግ ስራ አስፈፃሚና ለብልጽግና ወጣቶች ሊግ ዋና ጽ/ቤት ሲሆን የተቀሩት ከተሞች ሊግ አስተባባሪዎች ተጠሪ ለሆኑለት መዋቅር አስተባባሪ ኮሚቴ እና ሊግ ጽ/ቤት ይሆናል።

## አንቀጽ ፴፪.

### የከተማ የአስተዳደሩ ብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ አስተባባሪ ኮሚቴ አሰራር፣

፩. አስተባባሪ ኮሚቴው በየ፲፭ ቀኑ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል። በመደበኛ ስብሰባው የሚከተሉ ጉዳዮች ላይ ትኩረት ሰጥቶ ይወያያል።

ሀ) በሁለት ወር በከተማው አስተዳደሩ በወጣቶች ሊግ የተከናወኑ ስራዎችን የነበሩትን ጠንካራ እና ደካማ እንቅስቃሴዎች ግምገማ ያደርጋል።

ለ) ከግምገማው በመነሳት በቀጣይ ፪ ሳምንት ትኩረት የሚሰጣቸው አቅጣጫዎች ይቀይሳል፡

፪. የሩብ አመትና አመታዊ ግምገማዎችን ያካሂዳል ግብረ መልስ ይሰጣል የቀጣይ አቅጣጫ ያስቀምጣል።

፫. ምልዓተ ጉባኤው ፶+፩ ነው።

፬. ውሳኔዎች በተባበረ ድምጽ የሚፀድቁ ሆኖ ድምፅ መስጠት አስፈላጊ ሲሆን በ፶+፩ የተደገፈ ሀሳብ የአካሉ ውሳኔ ሆኖ ይፀድቃል። እኩል ድምፅ ከመጣ ሰብሳቢው የደገፈው ሀሳብ ፀዳቂ ይሆናል።

## አንቀጽ ፴፫.

የከተማ አስተዳደሩ የብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ ቅ/ጽ/ቤት አመራር ኮሚቴ የከተማው አስተዳደሩ የብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ ቅ/ጽ/ቤት ስራ አመራር ኮሚቴ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል።

፩. የብልጽና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ ቅ/ጽ/ቤት ኃላፊ ................................ ሰብሳቢ

፪. የብልጽና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ የፖለቲካና አደረጃጀት ዘርፍ ኃላፊ......... ምክትል

## አንቀጽ ፴፬.

### የከተማው አስተዳደሩ የብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ ቅ/ጽ/ቤት ስራ አመራር ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

1. የሊጉ ቅ/ጽ/ቤት በመተዳደሪያ ደንብ ላይ በተቀመጠው ተልዕኮ መሰረት የከተማው ወጣቶች የፖለቲካ፣ የአደረጃጀትና የህዝብ ግንኙነት ስራ ማዕከል ሆኖ ያገለግላል፡፡
2. ከብልጽግና ወጣቶች ሊግ ዋና ቅ/ቤት እና ከአስተባባሪ ኮሚቴዉ የሚወርዱ እቅዶችን መነሻ በማድረግ ከራሱ ከተማ ወጣቶች ሁኔታ ጋር በማጣጣም የፖለቲካና የአደረጃጀት ስራዎችን ያቅዳል፣ ፈፃሚውን አካል ኦረንቴሽን ሰጥቶ ያሰማራል፣ የስራውን አፈፃፀም ይከታተላል፣ ይመራል፣
3. መሰረታዊ ድርጅቶችና ህዋሳት በአደረጃጀታቸው ጠንካራና ተልዕኮ ፈፃሚ ሆነው እንዲወጡ የሚያስችል ድጋፍና አመራር መስጠትና ፖለቲካዊ ግንዛቤያቸውን እንዲዳብር ይሰራል፡፡
4. በከተማ አስተዳደሩ የሚካሄደውን የልማት፣ የመልካም አስተዳደር፣ የፖለቲካዊና አደረጃጀት ስራዎች ከወጣቶች አኳያ ያሉ መልካም ልምዶችን እና ድክመቶችን በመለየት መልካም ልምዶቹ እንዲስፋፉ ድክመቶቹ እንዲሻሻሉ ያደርጋል፡፡
5. የሊጉ የአሰራርና የአደረጃጀት መመሪያዎች፣ የማዕከላዊ ኮሚቴና የስራ አስፈፃሚ ውሳኔዎችና አቅጣጫዎች በከተማው አስተዳደሩ በስራ መተርጎማቸውን ይከታተላል ያስፈፅማል፣ ይገመግማል፣ ይፈጽማል፣
6. በከተማ አስተዳደሩ ውስጥ በሚገኙ የወጣት አባላት ማህደር፣ መረጃ የሊጉ ሰነዶች የሊጉ ንብረት እና በጀት በጥንቃቄ እንዲያዙና በአግባቡ ስራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፣
7. ብልጽግና ፓርቲ በህብረተሰቡ ዘንድ ያለው ተቀባይነት ጨምሮ የሊጉ አባላት ማህበረሰቡ ግንባር ቀደም እንዲሆኑ ፖለቲካዊ ብቃታቸው እንዲዳብር እና በአቋማቸዉ ጠንካራ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡
8. ሌሎች የወጣቶች አደረጃጀትን በማጠናከር ዴሞክራሲያዊ የወጣቶች አደረጃጀት እንዲሆኑና ጠንካራ የወጣቶች አመራሮች መፍለቂያ እንዲሆኑ ይሠራል፡፡
9. የሊጉ መሰረታዊ ድርጅትና የህዋስ አመራር አቅም ግንባታ ስራዎች ያሉበትን ደረጃና ችግሮች ይገመግማል፣ የመፍትሄ አቅጣጫ ያስቀምጣል፡፡
10. የሊጉን የፋይናንስ ስርዓት ይከታተላል የተለያዩ የሊጉን ገቢዎች ከፓርቲው ፋይናንስ ሰራተኞች ጋር በቅንጅት አፈጻሙን ተከታትሎ ሪፖርት ያቀርባል፡፡
11. አዲስ አበባ እና ድሬደዋ ብልጽግና ፓር ወጣቶች ሊግ ቅ/ጽ/ቤት ተጠሪነታቸው ለከተማ ለአስተዳደሩ ብልጽግና ወጣቶች ሊግ አስተባባሪ ኮሚቴና ለብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ ዋና ጽ/ቤት ይሆናል፡፡ ሌሎች ከተሞች ሊግ ቅ/ጽ/ቤቶች ተጠሪነታቸው ተጠሪ ለሆኑበት ክልል የብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ አስተባባሪና ሊግ ጽ/ቤት ይሆናል።

## አንቀጽ 35.

### የከተማ አስተዳደሩ የብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ ቅ/ጽ/ቤት አመራር ኮሚቴ አሰራር

1. የሊጉ ጽ/ቤት ሳምንታዊ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፣

፪. ምልዓተ ጉባኤው ፶0+፩ ነው፡፡

፫. ውሳኔዎች በተባበረ ድምጽ የሚፀድቁ ሆኖ ድምፅ መስጠት አስፈላጊ ሲሆን በ፶0+፩ የተደገፈ ሀሳብ የአካሉ ውሳኔ ሆኖ ይፀድቃል፡፡ እኩል ድምፅ ከመጣ ሰብሳቢው የደገፈው ሀሳብ የሚጸድቅ ይሆናል፡፡

፬. በሳምንቱ በከተማው/በአስተዳደሩ የወጣቶች ሊግ ፖለቲካዊና የአደረጃጀት ስራዎች የነበሩትን ዋና ዋና እንቅስቃሴዎች አስመልክቶ ግምገማ ያደርጋል፡፡ አቅጣጫም ያስቀምጣል፡፡

፭. አስተባባሪ ኮሚቴው በየ፲፭ ቀኑ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፣

**አንቀጽ ፫፮.**

የአዲስ አበባ ክፍለ ከተማ የብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ አስተባባሪ ኮሚቴ አደረጃጀት፣

የክፍለ ከተማ የብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ በከተማ አስተዳደሩ ብልጽግና ወጣቶች ሊግ አስተባባሪ ኮሚቴ የሚመደቡ/ የሚወከሉ 7 አባላት ያሉት ሆኖ ከመካከላቸው ሰብሳቢና ምክትል ሰብሳቢ ይመርጣሉ፡፡ ከሊጉ ጽ/ቤት አመራር አባላት በአስተባባሪ ባይመደቡም የአስተባባሪ ኮሚቴው መድረክ ተሳታፊዎች ይሆናሉ፡፡

**አንቀጽ ፫7.**

የክፍለ ከተማ ብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ አስተባባሪ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት፣

፩. ከከተማ የብልፅግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ አስተባባሪ ኮሚቴ በሚሰጠው አቅጣጫ መሰረት የክፍለ ከተማውን የሊጉን የአደረጃጀትና የፖለቲካ ስራዎች እንቅስቃሴ ይከታተላል፣ ይመራል፡፡

፪. የከተማ ብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ አስተባባሪ ያወጣውን እቅድ አፈፃፀም ስራን ተከታትሎ ያስፈፅማል፣ ይፈፅማል፡፡

፫. ሊጉ በፓርቲና በመንግስት ስራዎች የወጣቱን ተሳታፊነትንና ተጠቃሚነት መረጋገጡን ይከታተላል፤ ስራዎቹ ተቀናጅተው እንዲተገበሩ ያደርጋል፡፡

፬. በየወረዳ እና በየክፍለ ከተማ በወጣቶች አደረጃጀት እና በሊጉ የተገኙ መልካም ልምዶችን በመቀመር እንዲሰፋ ያደርጋል፣

፭. በክፍለ ከተማ የሚካሄዱ የሊጉን የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን ይከታተላል፣ የወጣቶችን ተሳትፎ ያረጋግጣል፣ ይመራል፣

፮. በክፍለ ከተማ ያሉትን የወጣት ሊግ አባላት፣ አመራሮች እና አጠቃላይ የወጣት የመንግስት አመራሮችን ፖለቲካዊ ብቃት በመገንባት ተልእኳቸውን የሚወጡ እንዲሆኑ የማብቃት ስራ ይሰራል፡፡

7. የወረዳ የወጣት ሊግ አስተባባሪ ኮሚቴና የሊግ አመራር አባላት ምደባ የውሳኔ ሃሳብ ቀጥሎ ላለው የፓርቲ ጽ/ቤት ያቀርባሉ፣ ሲፀድቅ ያሰማራሉ፣

፰. ስለ ስራው ክንውን ቀጥሎ ላለው የወጣቶች ሊግ አስተባባሪ ኮሚቴ ሪፖርት ያቀርባል፣ መልካም ልምዶችን

የማስፋት ስራው በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ይገመግማል፡፡ ለችግሮችም የመፍትሄ አቅጣጫ ያስቀምጣል፡፡

9. የመንግስትና የፓርቲ ስራዎች የወጣቶችን ተሳታፊነት እና ተጠቃሚነት በተገቢው መንገድ ተቀናጅተው ለማረጋገጥ እየተሰሩ መሆናቸውን ይገመግማል፡፡
10. የሊጉ የአሰራርና አደረጃጀት መመሪያዎች፣ የተቀመጡ አቅጣጫዎች በአግባቡ በስራ ላይ መዋላቸውን ይገመግማል፡፡
11. ተጠሪነቱ ለከተማው ወጣት ሊግ አስተባባሪ ኮሚቴና ለከተማዉ ሊግ ቅ/ጽ/ቤት ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 38.

### የክፍለ ከተማ የብልጽግና ፓርቲ የወጣት ሊግ አስተባባሪ ኮሚቴ አሰራር

1. በየሁለት ሳምንቱ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፣
2. ምልዓተ ጉባኤው 50+1 ነው፡፡
3. ውሳኔዎች በተባበረ ድምጽ የሚፀድቁ ሆኖ ድምፅ መስጠት አስፈላጊ ሲሆን በ50+1 የተደገፈ ሀሳብ የአካሉ ውሳኔ ሆኖ ይፀድቃል፡፡ እኩል ድምፅ ከመጣ ሰብሳቢው የደገፈው ሀሳብ ፀዳቂ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 39.

### የክፍለ ከተማ የብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ ቅ/ጽ/ቤት አመራር ኮሚቴ አደረጃጀት፣

የክፍለ ከተማ ብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ አመራር የሚከተለው ይሆናል

1. የብልፅግና ወጣቶች ሊግ ጽ/ቤት ኃላፊ …………………. ሰብሳቢ

## አንቀጽ 40.

### የክፍለ ከተማ ብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ ቅ/ጽ/ቤት አመራር ተግባርና ሀላፊነት

1. የክፍለ ከተማዉ ወጣቶች የፖለቲካ፣ የአደረጃጀትና የህዝብ ግንኙነት ስራ ማዕከል ሆኖ ያገለግላል፣
2. ከከተማ ብልጽግና ወጣቶች ሊግ ቅ/ጽ/ቤት የሚወርዱ እቅዶችን መነሻ በማድረግ ከራሱ ክፍለ ከተማ ወጣቶች ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማጣጣም የወጣቶችን ፖለቲካና የአደረጃጀት ስራዎችን ያቅዳል፣ ፈፃሚ አካላትን ለስራው ያዘጋጃል፣ ያሰማራል በስራው ሂደትም ተከታትሎ ይደግፋል፡፡
3. በክፍለ ከተማ የሚካሄደውን የልማት፣ የመልካም አስተዳደር፣ የአደረጃጀትና የፖለቲካዊና ፓርቲ ስራዎች ውስጥ በወጣቱ በኩል የሚታዩ መልካም ልምዶችን በመለየት በመቀመር እንዲስፋፉ ያደርጋል፡፡
4. የሊጉን አባላት የእለት ተእለት ግንባታ ስራን እየተከናወነ መሆኑንና በየወቅቱ ያለውን የአባላት ፖለቲካዊ ሁኔታ በመገምገም የግንባታ ስራው እያጠናከረ ይሄዳል፡፡ ጠንካራ የሊጉ ህዋስና መሰረታዊ ድርጅት አመራር የመፍጠር ስራን ያቅዳል፣ ተግባራዊ መሆኑንም ያረጋግጣል፣
5. በሊጉ እና በፓርቲው የሚካሄደውን የአባላትና የአመራር ስልጠና የወጣቱ ተሳትፎ ምጥጥን እንዲረጋገጥ ያደርጋል፣ ያደራጃል ስልጠናውም እንዲካሄድ ያደርጋል፡፡

6. በከተማው የሊግ ቅጽ/ቤት በሚሰጡ አቅጣጫዎች መሰረት የሊጉን ፕሮግራም፣ አቅጣጫዎች፣ የስራ እቅዶች እና አፈፃፀም በሚዲያና በህዝብ ግንኙነት መሳሪያዎች ለህዝብ ያስተዋውቃሉ፣
7. በሊጉ ልሳንና በሚወርዱ ጽሁፎች ላይ ተመስርቶ ለሚካሄደው የአባላት አቅም ግንባታ አባሎቻችን በተገቢው መሳተፋቸውንና ተደራሽነቱን ይከታተላል ስራውን ያስፈፅማል፣
8. የሊጉን የገቢ እና የፋናንስ ስራ በበላይነት ይመራል ከፓርቲው የፋይናንስ ሰራተኞች ግር ያለበትን ይከታተላል ሪፖርት ያቀርባል፡፡
9. የታቀዱ ስራዎች አፈጻጸም ይገመግማል፣ ድጋፍ ይሰጣል፡፡
10. ተጠሪነቱ ለክፍለ ከተማ ወጣቶች ሊግ አስተባባሪ ኮሚቴና ለከተማ ሊግ ቅ/ጽ/ቤት ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 41.**

## የክፍለ ከተማ ብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ ቅ/ጽ/ቤት አመራር አሰራር

1. የወረዳ የወጣት ሊጉን አመራር በቅርበት በመከታተል ተገቢውን ድጋፍ መስጠት፣
   ሀ) በየሩብ አመቱ ከወረዳ ወጣቶች ሊግ አመራር ኮሚቴ ጋር የስራ ግምገማ ያደርጋል፡
   ለ) በየወሩ ከወረዳ የወጣት ሊግ አመራር ጋር የአፈፃፀም ደረጃ የፅሁፍ ሪፖርት ተቀብሎ ተገቢውን ግብረ መልስና ድጋፍ ይሰጣል፡፡
   ሐ) በየሳምንቱ ከወረዳ ወጣቶች ሊግ ጋር የስልክ ልውውጥ በማድረግ ኢንፎርሜሽን ይቀበላል
   መ) አመታዊ የስራ አፈፃፀም ግምገማና የቀጣይ አመት እቅድ ለወረዳ ብልጽግና ወጣቶች ሊግ አመራር ኦረንቴሽን ይሰጣል፡፡

**አንቀጽ 42.**

## የአዲስ አበባ ከተማ የወረዳ/ድሬደዋ ቀበሌ የብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ አስተባባሪ ኮሚቴ አደረጃጀት፣

የወረዳ ብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ አሰተባባሪ ኮሚቴ አመራር ከወረዳዉ/ቀቤሌው ወጣቶች ሊግ ኮንፈረንስ የሚመረጥ/የሚወከል 7 አባላት ያሉት ኮሚቴ ሆኖ ከመካከላቸው ሰብሳቢና ምክትል ሰብሳቢ ይመርጣሉ፡ ፡ የወረዳው ወጣቶች ሊግ ጽ/ቤት አመራር በኮንፈረንሱ ካልተመረጠ/ች የአስተባባሪ ኮሚቴ መድረክ ተሳታፊ ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 43.**

የአዲስ አበባ ከተማ የወረዳ/የድሬደዋ ቀበሌ የብልጽና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ አስተባባሪ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊ

1. የሊጉ የፖለቲካ ስራና የወጣቶች የእለት ተእለት እንቅስቃሴ አጠቃላይ ሁኔታ ይከታተላል፣ ይመራል፣
2. የክፍለ ከተማዉ ብልጽግና ወጣቶች ሊግ ያወጣውን እቅድ መነሻ በማድረግ እንደወረዳው/ቀበሌው ተጨባጥ ሁኔታ የራሱን ዕቅድ ያቅዳል ያስፈጽማል፡፡
3. በወረዳ/በቀበሌ የሚካሄዱ የሊጉ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች ወጣቶችን ማሳተፍ መቻላቸውን ይከታተላል፣ ይመራል፣
4. የሊጉ፣ የፓርቲና የመንግስት ወጣት አመራር አካላትን ፖለቲካዊ ብቃት በመገንባት ተልእኳቸውን የሚወጡ እንዲሆኑ የማብቃት ስራ ይሰራል፡፡
5. ስለ ስራው ክንውን ቀጥሎ ላለው የወጣት ሊጉ አስተባባሪ ኮሚቴ ሪፖርት ያቀርባል፡፡
6. ተጠሪነቱ ለአድስአበባ ክፍለ ከተማ ወጣቶች ሊግ እና የድሬደዋ ቀበሌዎች ደግሞ ተጠሪነቱ ለከተማ አስተዳደሩ ወጣቶች ሊግ አስተባባሪ ኮሚቴ ይሆናል፡፡ ሌሎች ከተሞች ወጣቶች ሊግ አስተባባሪ ተጠሪነት ተጠሪ ለሆኑበት መዋቅር ወጣቶች ሊግ አስተባባሪ ኮሚቴ ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 44.**

የአዲስ አበባ ከተማ የወረዳ/የድሬደዋ አስተዳደር ቀበሌ የብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ አስተባባሪ ኮሚቴ አሰራር፣

1. የሊጉው አስተባባሪ ኮሚቴ ሳምንታዊ መደበኛ ስብሰባ ይኖረዋል፡፡
2. ምልአተ ጉባኤው 50+1 ነው፡፡
3. ውሳኔዎች በተባበረ ድምጽ መስጠት አስፈላጊ ሲሆን በ50+1 የተደገፈ ሀሳብ የአካሉ ውሳኔ ሆኖ ይፀድቃል፡፡ እኩል ድምፅ ከመጣ ሰብሳቢው የደገፈው ሀሳብ ፀዳቂ ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 45.**

የወረዳ የብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ ቅ/ጽ/ቤት አመራር አደረጃጀት፣

የወረዳ የብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ ቅ/ጽ/ቤት አመራር የሚከተለው ይሆናል

1. የብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ ቅ/ጽ/ቤት ኃላፊ ………………. ሰብሳቢ

**አንቀጽ 46.**

## የወረዳ/ቀበሌ የብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች አመራር ተግባርና ኃላፊነት

1. የወጣቶች የፖለቲካ፣ የአደረጃጀትና የህዝብ ግንኙነት ስራ ማዕከል ሆኖ ያገለግላል፡፡
2. ከወጣቶች ሊግ የሚወርዱ እቅዶችን መነሻ በማድረግ ከራሱ ወረዳ/ቀበሌ ከወጣቶች ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማጣጣም የፖለቲካና የአደረጃጀት ስራዎችን ያቅዳል፣ ፈፃሚ አካላትን ለስራው ያዘጋጃል፣ ያሰማራል በስራው ሂደትም ተከታትሎ ይደግፋል፣
3. በወረዳው/ቀበሌ የሚካሄደውን የልማት፣ የመልካም አስተዳደርና የሊጉንና ፓርቲ ስራዎችን ከመተግበር አኳያ በወጣቶች ዙሪያ ያሉ መልካም ልምዶችን በመለየትና በመቀመር እንዲስፋፋ ያደርጋል፡፡
4. የሊጉን አባላት የእለት ተእለት ግንባታ ስራን እየተከናወነ መሆኑንና በየወቅቱ ያለውን የሊጉን አባላት ፖለቲካዊ ሁኔታ በመገምገም የግንባታ ስራው እያጠናከረ ይሄዳል፡፡ ጠንካራ የሊጉ ህዋስና የመሰረታዊ ድርጅት አመራር የመፍጠር ስራን ያቅዳል ተግባራዊ መሆኑም ያረጋግጣል፡፡
5. በሊጉ የሚካሄደውን የአባላትና የአመራር የስልጠና ስራ ያጠናል፣ ያቅዳል፣ ያደራጃል ስልጠናውም እንዲካሄድ ያደርጋል፡፡
6. የስራ እቅዶችና አፈጻጸሙን በሚዲያና በህዝብ ግንኙነት መሳሪያዎች ለህዝብ ያስተዋውቃሉ፡፡
7. በሊጉ ልሳንና በወርዱ ጽሁፎች ላይ በሚካሄዱት ውይይቶች የወጣት አባላት የአቅም ግንባታ ስራዎችን ይመራል፣
8. ተጠሪነቱ ለወረዳ/ለቀበሌ ወጣቶች ሊግ አስተባባሪ ኮሚቴ እና ለክፍለ ከተማ /ለከተማ አስተዳደሩ የሊግ ቅ/ጽ/ቤት ኮሚቴ ይሆናል፣

## አንቀጽ 47.

## የወረዳ/የቀበሌ ብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ አመራር አሰራር

1. የወጣት ሊግ የቀበሌ/የመሰረታዊ ድርጅቶችና ህዋሳትን በቅርበት በመከታተል ተገቢውን ድጋፍ ይሰጣል፡፡ ቀጥሎ ላለው የወጣቶች ሊግ ጽ/ቤት ሪፖርት ይልካል፡፡

    ሀ. በየወሩ የወጣቶች ሊግ መሰረታዊ ድርጅቶችና ህዋሳት ያሉበት አፈፃፀም ደረጃ የፅሁፍ ሪፖርት ተቀብሎ ተገቢውን ግብረ-መልስና ድጋፍ ይሰጣል፡፡

    ለ. የሩብ ዓመት ተግባራት ይገመግማል፡፡

    ሐ. አመታዊ የስራ አፈፃፀም ግምገማና ቀጣይ አመት ዕቅድ ለሚመለከታቸው አካላት ኦሬንቴሽን ይሰጣል፡፡

## አንቀጽ 48.

## የፌደራል ተቋማት አደረጃጀት

1. ለፌደራል ተቋማት 7 አስተባባሪዎች በብልጽግና ወጣቶች ሊግ ዋና ጽ/ቤት አሰተባባሪ ኮሚቴ የሚመደቡ ይሆናል፡፡ ኮሚቴው ሰብሳቢ፣ ፖለቲካ ዘርፍ፣ አደረጃጀት ዘርፍ፣ ፋይናንስ ዘርፍ የሚሉ የስራ ክፍፍሎች

ይኖሩታል፡፡

፪. ተጠሪነታቸው ለብልጽግና ፓርቲ የወጣቶች ሊግ ዋና ጽ/ቤት ይሆናል፡፡

፫. የፌዴራል ተቋማት በወረዳ፤ በመ/ድርጅትና በሕዋስ የሚደራጁ ይሆናል፡፡

፬. በሶስት ወር አንዴ መደበኛ ስብሰባ ይኖራቸዋል፡፡

፭. አጠቃላይ አደረጃጀቱን የሚመሩበት አቅጣጫዎችንና ዕቅድ ያወጣሉ፡፡ በየሩብ አመቱ ሪፖርት እና የስራ አፈጻጸም ገምግመው አቅጣጫ ይሰጣሉ፡፡

፮. ከፌደራል ብልጽግና ፓርቲ የወጣቶች ሊግ የሚወርዱ አቅጣጫዎችንና ዕቅድን በመውሰድ እንዲፈጸሙ ያደርጋሉ

7. አደረጃጀቱም ህዋስ በየተቋሙ የሚመሰረት ሲሆን መሰረታዊ ድርጅቱ በአምስት ክላስተር ማለትም

- በኢኮኖሚ፣
- በማህበራዊ፣
- አስተዳደራዊ፤
- ውጭ ጉዳይ እና
- ፓርላማ አደረጃጀቶች ይደራጃል፡፡

፰. ክላሰተሩን የሚመሩ ከእያንዳንዳቸው ፭ አባላት ያሉት ኮሚቴ በአስተባባሪ ኮሚቴው ይመደባል፤ ሰብሳቢ፣ የፖለቲካ ዘርፍ፣የአደረጃጀት ዘርፍ እና ፋይናንስ ዘርፍ ከውስጣቸው ይመርጣሉ፡፡

ሀ) የሚደራጁ ምደባው የክላስተሮችን ስብጥር ማዕከል በማድረግ ይሆናል፤ ተጠሪነታቸው ለፌደራል ተቋማት አስተባባሪ ኮሚቴ ይሆናል፤

ለ) በየወሩ ተገናኝተው ስራ ይገመግማሉ ሪፖርት በየ፫ ወር ለአስተባባሪ ኮሚቴ ያቀርባሉ፡፡

## አንቀጽ ፵፱.

## የክልል/የዞን/የከተማ/የወረዳ/የክ/ከተማ/ልዩወረዳ፤ የአዲስ አበባ እና የድሬደዋ ሴክተር ተቋማት አደረጃጀት

፩. የክልል ሴክተር ተቋማት የሚመሩ 7 አስተባባሪ ኮሚቴ በክልል አስተባባሪ ኮሚቴ የሚወከሉ ይሆናል የሚመደቡት አስተባባሪዎች ከሶስቱ ክላስተር ማህከል ማድረግ ይገባል፡፡ ኮሚቴው ሰብሳቢ፣ ፖለቲካ ዘርፍ፣ አደረጃጀት ዘርፍ፣ ፋይናንስ ዘርፍ የሚሉ የስራ ክፍፍሎች ይኖሩታል፡፡

፪. የክልል ሴክተር ተቋማት አስተባባሪ ተጠሪነታቸው ለክልል አስተባባሪ ኮሚቴ እና ለክልሉ ብልጽግና ፓርቲ የወጣቶች ሊግ ቅ/ጸ/ቤት ይሆናል፡፡

፫. በ፫ት ወር አንዴ መደበኛ ስብሰባ ይኖራቸዋል፡፡

፬. የክልል ሴክተር ተቋማት ህዋስ በየተቋማቸውና መሰረታዊ ድርጅት በሶስት ክላስተር ማለትም

- በኢኮኖሚ፣

- በማህበራዊ እና
- አስተዳደራዊ ዘርፍ ይደራጃል፡፡

፭. ከክልል ብልጽግና ፓርቲ የወጣቶች ሊግ ጽ/ቤት እና አስተባባሪ ኮሚቴ የሚወርዱ አቅጣጫዎችንና ዕቅድን በመውሰድ እንዲፈጸሙ ያደርጋሉ፡፡

፮. የዞን/የከተማ/የወረዳ/የክ/ከተማ/ልዩ ወረዳ ሴክተር ተቋማት የሚመራው በየደረጃው በተቋቋመው የብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ አስተባባሪ ኮሚቴ ይሆናል፡፡

፯. የዞን/የከተማ/የወረዳ/የክ/ከተማ/ልዩ ወረዳ ሴክተር ተቋማት የመሰረታዊ ድርጅት አደረጃጀት እንደ ክልሉ ሴክተር ተቋማት ሆኖ የህዋስ አደረጃጀቱ በየራሳቸው ተቋምና የአባላት ቁጥሩ የሚያንስ ከሆነ የስራ ቅርበት ካላቸው ሴክተሮች ጋር የሚደራጅ ይሆናል፡፡

፰. የግንኙነት ጊዜ በወር አንድ ጊዜ ይሆናል፤

፱. አጠቃላይ አደረጃጀቱን የሚመሩበት አቅጣጫዎችንና ዕቅድ ያወጣሉ፡፡ በየሩብ አመቱ ሪፖርት እና የስራ አፈጻፀም ገምግመው አቅጣጫ ይሰጣሉ፡፡

# ክፍል አምስት

## በየደረጃው የሚኖር የብልጽግና ፓርቲ የወጣቶች ሊግ አስተባባሪ ኮሚቴ ውክልና፣

**አንቀፅ ፶.**

በብልፅግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ መተዳደሪያ ደንብ አንቀፅ ፳፮(፬) መሰረት በየደረጃው የሚዋቀሩ አሰተባባሪ ኮሚቴ እንዲሁም በአንቀፅ ፳፬ እና ፳፭ መሰረት ተግባርና ኃላፊነታቸውን የሚከውኑ ሆኖ፤ ለዚሁ ተግባራዊነት ኮንፈረንሶቹ በሚከተለው አግባብ በየደረጃው በሚኖር ውክልና ይመሰረታሉ፡-

፩. የክልል፤ የዞን፤ የወረዳ/ልዩ ወረዳ፤ የከተማ እና ቀበሌ የሊግ ኮንፈረንሶች ውክልናና ስብጥር በወጣቶችና በአባላት ብዛት ይወሰናል፤

፪. እያንዳንዱ አደረጃጀት የወጣቶችና የአባላት ብዛትን መሰረት በማድረግ በሚሰጠዉ ኮታ ላይ ተመስርቶ በየአደረጃጀቱ በአባላት ቀጥተኛ ተሳትፎ በሚካሄድ ምርጫ የወጣቶች ሊግ ኮንፈረንስ ተሳታፊዎቹን የሚወክል ይሆናል፣

፫. ለክልል ብልፅግና ወጣቶች ሊግ ኮንፈረንስ እንደ ክልል አባላት ብዛት ከ፫00 እስከ ፩፭00 አባላት ይሳተፋሉ፤

፬. በዞን ደረጃ እንደ ወጣቶች ሊግ አባላት ብዛት ከ፫00 እስከ ፩000 አባላት ይሳተፋሉ፤

፭. ልዩ ወረዳ ፤ ወረዳዎቸና ከተሞች እንደ ወጣቶች ሊግ አባላት ብዛት ከ፪00 እስከ ፩000 አባላት ይሳተፋሉ፤

6. በቀበሌ ደረጃ/በመሰረታዊ ድርጅት ደረጃ ያሉ ሁሉም አባላት በኮንፈረንሱ እዲሳተፉ ይደረጋል፤

## ክፍል ስድስት

### የብልጽግና ፓርቲ የወጣቶች ሊግ የመሰረታዊ ድርጅትና የሕዋሳት አደረጃጀት፣ ተልዕኮና አሰራር

**አንቀጽ ፭፩.**

የብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ መሰረታዊ ድርጅት አደረጃጀት

1. የብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ መሰረታዊ ድርጅት በክልል፣ በዞን፣ ከተማ፣ ወረዳና በቀበሌ ውስጥ የሚገኙ የወጣቶች ሊግ አባላትን የያዘ ከሁለት እስከ ስድስት የሆኑ የሊጉ ህዋሳትን በመያዝ የሚደራጁ ሆኖ፡-

ሀ. የመንግስት ሰራተኞች /ለክልል፣ ዞን/ልዩ ወረዳ፣ ከተማ፣ ወረዳና ቀበሌ መስርያ ቤቶች/ የሚሰሩ በየዘርፉ ማለትም የኢኮኖሚ፣ ማህበራዊ፣ አስተዳደራዊ መሰረታዊ ድርጅቶች የሚቋቋሙ ሆኖ፣ ተጠሪነታቸው በየደረጃው ላለ ወጣቶች ሊግ ጽ/ቤት ወይም ለሚዋቀረው አስተባባሪ ኮሚቴ ይሆናል፡፡

ለ. የብልጽግና ወጣቶች ሊግ አባል የሆኑ መምህራን፣ የአስተዳደር ሰራተኞች እና ተማሪዎች መሰረታዊ ድርጅት በተቋም ወይም በወረዳ፣ በቀበሌ (ለድሬዳዋ) የሚደራጅ ሆኖ ተጠሪነቱ ለሚገኝበት ቀበሌ (ለድሬዳዋ) ወይም ወረዳ ወጣቶች ሊግ ጽ/ቤት ይሆናል፡፡

ሐ. በሆስፒታል የሚሰሩ የወጣቶች ሊግ አባላት መሰረታዊ ድርጅት በተቋማቸው የሚቋቋም ሆኖ ተጠሪነቱ ለከተማ (አዲስ አበባ ክ/ከተማ) ወጣቶች ሊግ ጽ/ቤት ይሆናል፡፡

መ. የገጠር አርብቶና አርሶ አደሮች አደረጃጀት፣ የገጠር ባለሙያዎች በአንድ የወጣቶች ሊግ መሰረታዊ ድርጅት ይደራጃሉ፡፡ ተጠሪነታቸው ለወረዳቸው ወጣቶች ሊግ ጽ/ቤት ይሆናል፡፡

ሠ. የከተማ ነዋሪዎች መሰረታዊ ድርጅቶች በመኖሪያ ለከተማቸው/ወረዳ የሚደራጁ ሲሆን፣ ተጠሪነታቸውም ለከተማቸው/ወረዳ ወጣቶች ሊግ ጽ/ቤት ይሆናል፡፡

ረ. በአንድ ዘርፍ የተሰማሩ ወይም አንድ አካባቢ ተደራጅተው የሚሰሩ ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ቁጥራቸው በቂ ከሆነ በአንድ የወጣቶች ሊግ መሰረታዊ ድርጅት ታቅፈው ይንቀሳቀሳሉ፡፡ ቁጥራቸው አነስተኛ ከሆነ ተመሳሳይ ባህርይ ያላቸው በክላስተር ይደራጃሉ፡፡ ተጠሪነታቸው ለከተማቸው ወይም ወረዳ ወጣቶች ሊግ ጽ/ቤት ይሆናል፡፡

ሰ. የላብ አደሮች ወጣቶች ሊግ መሰረታዊ ድርጅት በሚሰሩባቸው ተቋማት ወይም በኢንዱስትሪ ክላስተር የሚቋቋሙ ሆነው፣ ተጠሪነታቸው ለከተማቸው/ወረዳ ወጣቶች ሊግ ጽ/ቤት ይሆናል፡

2. በየትኛውም ደረጃ የሚቋቋሙ ወጣቶች ሊግ መሰረታዊ ድርጅቶች ከሁለት እስከ ስድስት ህዋሳት ያሉት ሆኖ ከ22 እስክ 210 አባላት ያሉት ይሆናል፡፡

3. እያንዳንዱ መሰረታዊ ድርጅት 10-12 አባላት ባሉት የመሰረታዊ ድርጅት አመራር ኮሚቴ ይመራል፡ አመራሩም በመሰረታዊ ድርጅት ኮንፈረንስ ይመረጣል፡፡

፬. የሚመረጡት የአመራር አባላት የሚከተሉትን መሰረታዊ መስፈርቶች ማሟላት አለባቸው፡፡

ሀ. በተሰማራበት የስራ መስክ ባስመዘገበው የስራ ውጤት ለሌሎች አርአያ የሆነ/ች፣

ለ.በሙያውና በስነ-ምግባሩ ምስጉን የሆነ/ችና የተሰጠውን ተልዕኮ በብቃት የሚወጣ/የምትወጣ፣

ሐ. ለውጡን ወደፊት ይዞ የመሄድ ራዕይ ያለው/ያላት አባል ፣

መ. የወጣቶች ሊግ እና የፓርቲውን አሰራሮች በማወቅና ተግባራዊ በማድረግ የተሻለ እንቅስቃሴ የሚያደርግ/የምታደርግ ፣

ሠ. በተሰማራበት/ችበት ስራ ሳይወሰን ለወጣቶች ሁለተናዊ ተጠቃሚነት የልማትና የመልካም አስተዳደር እንቅስቃሴዎች ዙሪያ ጉልህ አስተዋጽኦ ያበረከ/ተች፣

ረ. በአካባቢው ሕብረተሰብና የስራ ጓደኞቹ/ቿ ዘንድ በስርዓትና በማሕበራዊ ግንኙነት የተሻለ ተቀባይነት ያተረፈ/ች፣

ሸ. የመሰረታዊ ድርጅቱ አመራር አባላት አስከተቻለ ድረስ ከልዩ ልዩ ህዋሳት አባላት መካከል እንዲመረጡ ይደረጋል፡፡

ቀ. የብልጽግና ፓርቲ የወጣቶች ሊግ መሰረታዊ ድርጅት አመራር ኮሚቴ የራሱን ሰብሳቢ፣ ምክትል ሰብሳቢ፣ ፀሀፊና ገንዘብ ያዥ ይመረጣል፡፡ በስሩም የሚከተሉት ንዑሳን ኮሚቴዎች ይኖሩታል፡፡

ሀ. የፖለቲካ ስራዎች ንኡስ ኮሚቴ

ለ. የአደረጃጀት ስራዎች ንኡስ ኮሚቴ

ሐ. የፋይናንስ ንኡስ ኮሚቴ

**አንቀፅ ፭፪.**

የብልጽግና ፓርቲ የወጣቶች ሊግ መሰረታዊ ድርጅት ተልዕኮ፡-

፩. በሚኖሩበት አካባቢ ውስጥ የሚካሄዱትን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ የልማት ጉዳዮች፣ የመልካም አስተዳደርና የሰላም ተግባራት በብቃት እንዲያንቀሳቀሱ የወጣቶች ሊግ አባላትን ማብቃት፡

፪. የወጣቶች ሊግ አባላትና የወጣት አመራር አካላት ፖለቲካዊና ስነ-ምግባራዊ ብቃት ማጎልበቻ፣ የተሞክሮ መለዋወጫ መድረክ ሆኖ ማገልገል፡፡

፫. በልማት፣ በመልካም አስተዳደርና በፖለቲካ ስራዎች ያሉትን መልካም ልምዶች በእያንዳንዱ የወጣት ሊግ አባል በተሟላ መልኩ ማስፋፋት፡፡

፬. በማያቋርጥ አኳኋን የአዳዲስ የወጣት ሊግ አባላት ምልመላ እንዲካሄድ ተገቢውን አመራርና ድጋፍ ይሰጣል፣ አባላት ጠንካራ ፖለቲካዊ ህይወት እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡

**አንቀፅ ፭፫.**

የብልጽግና ፓርቲ የወጣቶች ሊግ መሰረታዊ ድርጅት አመራር ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

፩. የብልጽግና ፓርቲ በወጣቶች ሊግ መሰረታዊ ድርጅት ኮንፈረንስ የፀደቀውን ዕቅድ ዝርዝር አፈፃፀም

በማዘጋጀት ይፈፅማል፣ ያስፈፅማል፣

2. በልማት፣ በመልካም አስተዳደር በአደረጃጀትና በፖለቲካ ስራዎች የወጣቶች ተጠቃሚነት መረጋገጡን እና ያሉትን መልካም ልምዶች በእያንዳንዱ ወጣቶች ሊግ አባልና መዋቅራቸው ደረጃ የማስፋት ስራ በተቀመጠው አቅጣጫ መሰረት መከናወኑ ያረጋግጣል፣
3. የብልጽግና ፓርቲ የወጣቶች ሊግ ህዋስ አመራርን ፖለቲካዊና የአመራር አቅም በሴሚናሮችና በግምገማ ነክ ስልጠናዎች በቀጣይነት የመገንባት ስራ ይሰራል፣
4. የንዑሳን ኮሚቴዎችን እንቅስቃሴ ይከታተላል፣ አመራር ይሰጣል፣
5. የሊጉን ህዋሳት ውይይት አፈፃፀምን ይከታተላል። በውይይቱ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ ጉዳዮችን በመለየት እንዲሰራበት ያደርጋል። ፈጣንና ውጤታማ የግብረ መልስ ስርዓት እንዲኖር ያደርጋል፣
6. በስሩ የተደራጁ ህዋሳት ጠንካራ ሆነው እንዲንቀሳቀሱ አስፈላጊውን አመራር ይሰጣል።
7. አጠቃላይ አባላት ተልእኮአቸውን በአግባቡ መወጣታቸውን ይከታተላል፣ በዚህ ረገድ ሊወሰዱ የሚገባቸው እርምጃዎች እንዲወሰዱ ያደርጋል።
8. በወጣቶች ሊግ መተዳደርያ ደንብ መሰረት ለመሰረታዊ ድርጅት የተሰጡ ተግባርና ኃላፊነቶች ያከናውናል፤ መተዳደርያ ደንቡ በሚሰጠው ስልጣን ክልልም የአባላትን ቅጣት ይወስናል።
9. ለወጣቶች ሊግ መሰረታዊ ድርጅት ኮንፈረንስ በየሦስት ወሩ፣ አንድ እርከን ቀጥሎ ላለው ሊግ ጽ/ቤት ወይም ለኮሚቴ በየወሩ የተከናወነውን ፖለቲካዊና አደረጃጀት እንቅስቃሴ ሪፖርት ያቀርባል።
10. የአባላትን ማህደር በአግባቡ መያዙን ያረጋግጣል።
11. ለወጣቶች ሊግ መሰረታዊ ድርጅት ኮንፈረንስ የሚያስፈልጉ ዝግጅቶን ያከናውናል።
12. የአባላት መዋጮ በደረሰኝ ሰብስቦ ለሚመለከተው ክፍል ገቢ ያደርጋል።
13. ተጠሪነቱ ለመሰረታዊ ድርጅት ኮንፈረንስና በየደረጃው ላለው ወጣቶች ሊግ ጽ/ቤት ወይም ለሚዋቀረው ኮሚቴ ይሆናል።

## አንቀጽ 54.

### የብልጽግና ፓርቲ የወጣቶች ሊግ መሰረታዊ ድርጅት ሰብሳቢ ተግባርና ኃላፊነት

1. የወጣቶችን ሊግ መሰረታዊ ድርጅት ፖለቲካዊና አደረጃጀት ስራ ወጣቶች ይመራል ፣ ያስተባብራል።
2. የወጣቶች ሊግ ህዋስ አመራር ፖለቲካዊ አቅም ግንባታ ስራን ይከታተላል፣ በበላይነት ይመራል።
3. የሊጉ ህዋሳት ጠንካራ የተደራጁ ሆነው እየተንቀሳቀሱ መሆናቸውን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል።
4. የአመራር ኮሚቴውንና የመሰረታዊ ድርጅቱን ኮንፈረንስና አስቸኳይ ስብሰባዎች በሰብሳቢነት ይመራል።
5. ለስብሰባዎቹ የሚሆን የስራ አፈፃፀም ሪፖርት ወዘተ... ያዘጋጃል ወይም የሚመለከታቸው ኮሚቴዎች እንዲያዘጋጁ በማድረግ ለስብሰባው ያቀርባል።
6. ከበላይ አካል ጋር ኮሚቴውን በመወከል ይገናኛል። ለበላይ አካል ሪፖርት ያቀርባል፤ ከበላይ አካል

መመሪያ ይቀበላል፡፡

7. ተጠሪነቱ ለመሰረታዊ ድርጅት አመራር ኮሚቴና ለየመዋቅራቸው ወጣቶች ሊግ ጽ/ቤ ይሆናል፡፡

**አንቀጽ ፶፭.**

የምክትል ሰብሳቢ ተግባርና ኃላፊነት

1. ሰብሳቢው/ዋ በማይኖርበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል፣
2. በፖለቲካ ስራዎች ንኡስ ኮሚቴ የተቀመጡ ስራዎችን በበላይነት ይመራል ፤ያስተባብራል፡፡
3. ከሰብሳቢው የሚሰጠውን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡
4. ተጠሪነቱ ለሰብሳቢውና ለፖለቲካ ኃላፊው ይሆናል፡፡

**አንቀጽ ፶፮.**

የፀሐፊ ተግባርና ኃላፊነት

1. ለአደረጃጀት ንኡስ ኮሚቴ የተቀመጡ ስራዎችን በበላይነት ይመራል ኮሚቴውን ያስተባብራል፤
2. የመሰረታዊ ድርጅቱና የአመራር ኮሚቴዎችን ሰነድ ይይዛል፡፡
3. ከሰብሳቢው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል ፡፡
4. ተጠሪነቱ ለሰብሳቢው እና አደረጃጀት ኃላፊው ይሆናል፡፡

**አንቀጽ ፶፯.**

**የመ/ድርጅት** የፖለቲካ ሥራዎች ንኡስ ኮሚቴ አመራር አባላት አደረጃጀት

1. ንኡስ ኮሚቴው አራት የአመራር አባላት ሲኖሩት እነርሱም

   ሀ. የመሰረታዊ ድርጅቱ ምክትል ሰብሳቢ ............................ ሰብሳቢ

   ለ. አንድ የመሰረታዊ ድርጅት አመራር ኮሚቴ አባል ............. ም/ሰብሳቢ

   ሐ. ሁለት የመሰረታዊ ድርጅት አመራር ኮሚቴ አባል ............ አባል ይሆናሉ፡፡

**አንቀጽ ፶፰.**

## የንኡስ ኮሚቴው ዋና ዋና ተግባራት

1. በዚህ ንኡስ ኮሚቴ ውስጥ የአባላት ፖለቲካዊ የዕለት ተዕለት ግንባታ ስራ፣ የስልጠና፣ ኮንፈረንስ፣ የአባላት ዓቅም ግንባታ ስራ፣ በልሳናትና በብልፅግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ መፅሔት ላይ የሚደረግ ውይይት ይመራል፣

ሀ.የወጣት ሊግ አባል ብቁ ፖለቲካዊ ግንዛቤና አቋም ኖሮአቸው ተልእኮዎቹን ለመፈፀም የሚያስችላቸው ሁኔታ ላይ እንዲገኙ ተከታታይ ውይይትና ተግባር ውስጥ እንዲገባ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋሉ፣

ለ. እያንዳንዱ አባልና አመራር መልካም ልምዶችን ለማስፋፋትና ለመተግበር የሚያስችላቸው የአስተሳሰብ ዝግጁነት እንዲኖራቸው ይሰራሉ፣

2. የህዋስና የመሰረታዊ ድርጅት አመራሮች አቅም ግንባታ ስራ እንዲሰራ ያደርጋሉ፣

   ሀ. የፖለቲካ ስራ ዘርፍ በሚያወጣው እቅድ መሰረት መከናወኑን ይከታተላሉ፡፡

   ለ. የተገኘውን ውጤትና የሚታዩ ችግሮችን በመከታተል ይገመግማሉ፣ መፍትሔ እንዲሰጥ ያደርጋሉ፡፡

3. አባላት በልሳናት እና በብልፅግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ መፅሔት ላይ ውይይት እንዲያካሂዱ ማድረግ፡፡

   ሀ. ለወጣቶች ሊግ መሰረታዊ ድርጅት አባላት መወያያ የሚሆኑ በልሳናትና በብልፅግና ወጣቶች ሊግ መፅሔት ፅሁፎችን እቅድ ያዘጋጃል፡፡

   ለ በእቅዱ መሰረት ልሳናት በወቅቱ የሚመጡበትን ስርዓት ይዘረጋል በዚሁ መሰረት መድረሳቸውን ያረጋግጣል፣

   ሐ. የህዋሳት የውይይት ፕሮግራሞችን ያዘጋጃል፣ በፕሮግራማቸው መሰረት ውይይት ማካሄዳቸውን ይከታተላል፡፡

   መ. በህዋሳት ውይይት ላይ የተነሱ ጉዳዮችን ከህዋሳት የፖለቲካ ስራ ሃላፊዎች በመቀበል ምላሽ ይሰጣል፡፡

   ረ. ከንኡስ ኮሚቴው አቅም በላይ የሆነውን ለመሰረታዊ ድርጅት አመራርና ለፖለቲካ ስራ ዘርፍ በማቅረብ አቅጣጫ ይቀበላል፣ ለህዋሳት ያሳውቃል፡፡

4. በመሰረታዊ ድርጅት ደረጃ ኮንፈረንስ እንዲካሄድ በማድረግ አባላት በኮንፈረንስ መድረኮች ላይ ተገኝተው በሚገባ መወያየታቸውንና ግንዛቤ መያዛቸውን ይከታተላል፣

5. የተለያዩ ሴሚናሮች ለወጣቶች ሊግ አባላት እንዲሰጡ ማድረግ፣

   ሀ. የመወያያ ርእሶችንና ሰነዶች በወቅቱ መድረሳቸውን እንዲሁም አወያዮች መሟላታቸውን ይከታተላል፣

   ለ. በበላይ አካል በሚሰጠው እቅድ መሰረት አባላት በተሟላ መልኩ በሴሚናሮች ላይ መሳተፋቸውንና በቂ ፖለቲካዊ ግንዛቤ ማዳበራቸውን ይከታተላል፣

6. ስልጠናዎች እንዲሰጡ ማድረግ፡-

   ሀ. የሚካሄዱ ስልጠናዎችን ያደራጃል፣

   ለ. በበላይ አካል የሚካሄዱ ስልጠናዎች ሲኖሩ የምልመላና የሰው ሃይል ዝግጅት ስራዎችን ያከናውናል፣

ሐ. የተሰጡ ስልጠናዎችን ውጤት ተከታትሎ ይገመግማል፣ ክፍተቶችን ይለያል፣ ሪፖርት ያቀርባል፣

መ. ወደፊት ሊሰጡ ስለሚገባቸው ስልጠናዎች ለሊጉ መሰረታዊ ድርጅት አመራር ሃሳብ ያቀርባል፣

7. ከፖለቲካ ኮሚቴ ጋር የስራ ግንኙነት በመፍጠር ድጋፍ ያገኛል፣ ሪፖርትም ያቀርባል የንኡስ ኮሚቴውን ስራ በተመለከተ ከፖለቲካ ኮሚቴ ጋር እየተገናኘ አስፈላጊውን የመረጃ ልውውጥ ያደርጋል፣ ድጋፍ ያገኛል፣

8. ተጠሪነቱ ለመሰረታዊ ድርጅት ሰብሳቢና ለፖለቲካ ኮሚቴ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 59.

### የአደረጃጀት ስራዎች የንኡስ ኮሚቴ አደረጃጀትና አሰራር

1. ኮሚቴው አራት የአመራር አባላት ሲኖሩት እነሱም፡-

ሀ. የመሰረታዊ ድርጅቱ ፀሀፊ ....................................... ሰብሳቢ

ለ. አንድ የመሰረታዊ ድርጅት አመራር ኮሚቴ አባል .......... ምክትል ሰብሳቢ

ሐ ሁለት የመሰረታዊ ድርጅት አመራር ኮሚቴ አባል .......... አባል ይሆናሉ፡፡

## አንቀጽ 60.

### የአደረጃጀት ስራዎች ንኡስ ኮሚቴ ዋና ዋና ተግባራት

የንኡስ ኮሚቴውን መረጃዎችና የአባላትን የግል ማህደር መያዝ፣ የአደረጃጀትና አሰራር መመሪያዎችን ተፈፃሚነት መከታተልና እያንዳንዱ አባል በአደረጃጀት ታቅፎ ተልዕኮዎቹን እየፈፀመ መሆኑን፣ አዳዲስ የአፈፃፀም ልምዶችን መቀመርና ወደ ሌሎች የማስፋፋት ስራ ይሰራል፡፡ የአደረጃጀት ስራዎች ንኡስ ኮሚቴ የሚከተሉት ዋና ዋና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. አባሉ የተደራጀና ጠንካራ አደረጃጀት ሆኖ ተልዕኮዎቹን የሚወጣ መሆኑን የሚያረጋግጥ ስራ ማቀድና ማከናወን፣

ሀ. እያንዳንዱ አባል በተለይም የመሰረታዊ ድርጅትና የሕዋስ አመራር በተልዕኮው ላይ ግልፅ የሆነ፣ ፖለቲካዊ ግንዛቤው ከፍ ያለና ጠንካራ አቋም ያለው፣ በተግባር ራሱ ሰርቶና ተጠቅሞ ለሌሎች በአስተማሪነቱ የሚጠቀስ እንዲሆን ያደርጋል፣

ለ. አባላችን የተደራጀና እንደ አንድ ተልዕኮ ፈፃሚ ኃይል ጠንካራ ተጽዕኖ እያሳረፈና ለውጥ እያመጣ መሆኑን ማረጋገጥ፣

ሐ. አባሉ ተደራጅቶ ወደ ስራ ለመግባትና የሚፈለገውን ውጤት ለማምጣት ያሉበትን ችግሮች በየጊዜው እየገመገመ የመፍትሄ ሃሳብ ያቀርባል፣ የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፡፡

2. የአደረጃጀትና የአሰራር መመሪያዎች በአባላት ታውቀው ስራ ላይ እንዲውሉ የሚያስችል ዲስፕሊን መፍጠር፣

   ሀ. አባላት በአደረጃጀትና አሰራር መመሪያዎች ላይ በቂ ግልጽነት የያዙ መሆናቸውን ያረጋግጣል፣ ካልያዙ ስልጠና እንዲያገኙ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣

   ለ. የአደረጃጀትና የአሰራር መመሪያዎች በትክክል ስራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ ችግሮች ካሉ ያስተካክላል።

3. የወጣቶች ሊግ አባላት አደረጃጀት መፍጠርና ማጠናከር

   ሀ. ሁሉም የሊግ አባላት በመሰረታዊ ድርጅትና በህዋስ አደረጃጀቶች ውስጥ መደራጀታቸውን ያረጋግጣል፣

   ለ. አደረጃጀቶቹ የአባላትን ግንዛቤ በማሳደግና ተግባራዊ እንቅስቃሴያቸውን በመምራት በኩል ወሳኝ ሚና እንዳላቸው በትክክል እንዲገነዘቡ ያደርጋል፣

   ሐ. አባላት ሚናቸውን እየተጫወቱ መሆናቸውን መከታተልና ማረጋገጥ፣ ለሚታዩ ችግሮችም መፍትሄ ያፈላልጋል፣

4. እያንዳንዱ አባል ተልዕኮዎቹን ስራ ላይ ማዋሉን ክትትል በማድረግ የእያንዳንዱን አባል ደረጃ መለየት፣ ድጋፍ ማድረግ፣

   ሀ. እያንዳንዱ አባል ተልዕኮዎቹን በግልጽ መያዙን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል

   ለ. በዚሁ መሰረት ስራ ላይ ማዋሉን በጥብቅ ክትትል ይለያል፣

   ሐ. በለውጡ አፈፃፀም ውጤቱ ላይ በመመስረት በየጊዜው ለእያንዳንዱ አባል ደረጃ እንዲወጣለት ያደርጋል፣

   መ. አባሉ ግንባር ቀደም ሚናውን ስለመወጣቱም በአባላት እንዲመዘንና የማጠናከሪያ ድጋፍ ይሰጣል፣

   ሠ. ግንባር ቀደም ሚናቸውን የማይወጡ ካሉ ተገቢውን ማስተካከያ ያደርጋል፣

5. የወጣቶች ሊግ አባላት ማህደር በየጊዜው እየተሞላ መያዙን ማረጋገጥ

   ሀ. እያንዳንዱ አባል የግል ማህደር የተዘጋጀለት መሆኑን ያረጋግጣል፣

   ለ. በየ6 ወሩ በሂስና ግለሂስ ላይ የተመሰረተ የታደሰ ማህደር መዘጋጀቱን ያረጋግጣል፣ የአባሉ የግል ማህደር ለተፈላጊ ስራ እንዲውል ያደርጋል።

6. ከአደረጃጀት ኮሚቴ ጋር የስራ ግንኙነት በመፍጠር ድጋፍ ያገኛል፣ ሪፖርትም ያቀርባል፤ የንኡስ ኮሚቴውን ስራ በተመለከተ ከአደረጃጀት ጋር በየጊዜው እየተገናኘ አስፈላጊውን የመረጃ ልውውጥ በማድረግ ድጋፍ ያገኛል፣

7. ተጠሪነቱ ለመሰረታዊ ድርጅት ሰብሳቢና ለአደረጃጀት ኮሚቴ ይሆናል፣

## **አንቀጽ 61.**

## የመ/ድርጅት ፋይናንስ ንኡስ ኮሚቴ አደረጃጀትና ዋና ዋና ተግባራት

## አደረጃጀትና አሰራር

ሀ. የመሰረታዊ ድርጅቱ ገንዘብ ያዥ ......................................ሰብሳቢ

ለ. አንድ የመሰረታዊ ድርጅት አመራር ኮሚቴ አባል .......... ምክትል ሰብሳቢ

ሐ አንድ የመሰረታዊ ድርጅት አመራር ኮሚቴ አባል .......... አባል ይሆናሉ፡፡

## ዋና ዋና ተግባራት

1. በሊጉ የገቢ እቅድ ማዘጋጀት፣ ገቢ ማሰባሰብና ማስገባት ዙሪያ የስራ ክፍፍል ይኖራቸዋል፡፡
2. የሊጉንን አመታዊ ገቢ ዕቅድ ማዘጋጀት እና በእቅዱ መሰረት ማሰባሰብ፣
3. የሊጉ ገቢዎች በህጋዊ ደረሰኝ መሰብሰባቸውን ያረጋግጣል ሪፖርት ለሊግ ጽ/ቤት ያደርጋል፣
4. የልሳናትና የሊጉ መፅሔት የመፅሄት ሽያጭ ገቢ ያደርጋል፣
5. ከብልፅግና ፓርቲ የፋይናንስ ንኡስ ኮሚቴ ጋር ተቀናጅቶ ይስራል
6. ተጠሪነቱ ለመሰረታዊ ድርጅት ሰብሳቢና ለወጣቶች ሊግ ጽ/ቤት ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 62.

### የብልጽግና ፓርቲ የወጣቶች ሊግ መሰረታዊ ድርጅት አሰራር

1. የወጣቶች ሊግ መሰረታዊ ድርጅት ኮንፈረንስ በተሳካ ሁኔታ እንዲካሄድ ያደርጋል፣
2. የወጣቶች ሊግ መሰረታዊ ድርጅት ኮንፈረንስ የለውጥ ሂደት ያለበት ደረጃ በቁልፍ አጀንዳነት ተይዞ ይገመገማል፣
3. የኮንፈረንስ ጊዜ ቢያንስ ከ1 ወር በፊት አስቀድሞ እንዲታወቅ ይደረጋል፡፡ በተቻለ መጠን ኮንፈረንሱን ተከታታይ የሆኑ የበአል ቀናትን ግምት ውስጥ በማስገባት እንዲጠራ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡
4. የመሰረታዊ ድርጅት ኮንፈረንስ በየሶስት ወሩ የሚካሄድ ይሆናል፣
5. የኮንፈረንስ አጀንዳዎች ምን ሊሆኑ እንደሚገባ ተመካክሮ ለህዋሳት ማሳወቅና ህዋሳት የሚፈልጉት አጀንዳ ካለ እንዲጠቀሙ ማድረግ ይኖርበታል፣
6. ልዩ ልዩ ንኡሳን ኮሚቴዎች የስራ አፈፃፀማቸውን በተመለከተ የየራሳቸውን ሪፖርት በአጭሩ እንዲያዘጋጁና በሪፖርቱ የቀጣይ እቅድም መነሻዎች እንዲቀርቡ ይደረጋል፡፡
7. ከበላይ አካል በኮንፈረንሱ ላይ ቢታዩ ይጠቅማሉ የሚባሉ አጀንዳዎችን በመቀበል ከየመዋቅራቸው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር አጣጥሞ ለውይይት እንዲቀርቡ ይደረጋል፣
8. በኮንፈረንስ መድረክ ላይ አጀንዳዎችን በማፅደቅ በቅደም ተከተል ውይይት ይደረግባቸዋል፣
9. አባላት በየርዕሱ ነፃ ሆነው ሀሳባቸውን እንዲገልፁ፣ እንዲቃወሙም ሆነ እንዲደግፉ ሰፊ እድል መስጠትና በበቂ ሁኔታ ከተወያዩ በኋላ ወደ ውሳኔ ሃሳብ የማምራት አግባብን መከተል ይገባል፣
10. የውሳኔ ሃሳቡ በፅሁፍ ተዘጋጅቶ በንባብ እንዲቀርብና በድምፅ እንዲወሰን ይደረጋል፣
11. በኮንፈረንሱ ማጠቃለያ ላይ የጋራ የአቋም መግለጫ ማውጣት፣ የአቋም መግለጫው ሁሉንም የውሳኔ

ሃሳቦች በአጭር በአጭሩ እንዲይዝ በማድረግ ለህዋሳት ሃላፊዎች ኮፒ እንዲደርስ ማድረግ ይገባል፣

12. በኮንፈረንሱ ማጠቃለያ ላይ የአመራሩ ምዘና ለአባሉ እንዲቀርብ ተደርጎ የሚጨመር ወይም የሚስተካከል ካለ እንዲስተካከል ይደረጋል፣
13. የአመራር ምርጫ በየአመቱ መጀመሪያ በሚካሄደው ኮንፈረንስ ይሆናል፣
14. አባላት ወይም የበላይ አካል አስቸኳይ ኮንፈረንስ ሲጠይቁ ለመላ አባላት ህዋሳት ስብስባ ላይ አሳውቆ ግማሽ ያህሉ ከደገፈው እንዲካሄድ ይደረጋል፣
15. የኮንፈረንሱ አጠቃላይ ሂደት በቃለ-ጉባኤ እንዲያዝ ይደረገል፣
16. የኮንፈረንሱ ምልአተ ጉባዔ ከመሰረታዊ ድርጅቱ አባላት ከግማሽ በላይ /50%+1/ ሲገኙ ይሆናል፣
17. ኮንፈረንሱ በድምፅ ብልጫ የሚያስተላልፋቸው ውሳኔዎች በኮንፈረንሱ ከተገኙት ውስጥ ከግማሽ በላይ /50%+1/ የደገፉት ሊሆን ይገባል፡፡

## አንቀጽ 63.

### በኮንፈረንሱ ውሳኔዎች መሰረት ተግባርን መምራት

1. ኮንፈረንሱ ከተጠናቀቀ በኋላ አመራሩና መላ አባላት በየአደረጃጀታቸው አማካይነት ፈጥነው ወደ ስራ መግባትና የተቀመጡትን ተግባራት ለማስፈፀምና ግቡን ለማሳካት መረባረብ ይገባቸዋል፣
2. የጋራ ስራዎችን በስምምነታቸው መሰረት በከፍተኛ የሃላፊነት መንፈስ ይፈፅማሉ፣
3. የመልካም አስተዳደርና ሌሎች ተግባራትን በእቅዱ መሰረት መፈፀም፣
4. ከእያንዳንዱ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ብቁ ትምህርት መውሰድ፣ በአመራር ደረጃ ምርጥ የአባላት ልምዶችን እየለቀሙ ለሁሉም ማሳወቅና የአፈፃፀም ስልቶች የጋራ ሃብት እንዲሆኑ ማድረግ፣
5. የስራ አፈፃፀም ሂደቱን በተቀመጡ ጊዜዎች በመደበኛነት መገምገምና አስፈላጊውን የእቅድ ማስተካከያ እያደረጉ ስራውን በጥራት መስፈፀም ይጠበቅባቸዋል፡፡

## አንቀጽ 64.

### በብልፅግና ወጣቶች ሊግ አመራር ደረጃ የመማማር አሰራርን ጥቅም ላይ ማዋል

1. አመራሩ የስራ አፈፃፀሙን መሰረት በማድረግ መማማር ፕሮግራም በየወሩ ያካሂዳል፣
2. በየሶስት ወሩ በተራ ቁጥር 1 የደረሰበትን ውጤት ለወጣቶች ሊግ መሰረታዊ ድርጅት በአጭሩ አቅርቦ ያስገመግማል፡፡ ከወጣቶች ሊግ አባላት የሚቀርቡ ትችቶች ካሉ ተቀብሎ ምላሽ ይሰጣል፣

፫. በሁሉም ደረጃ የሚካሄደው መማማር ፕሮግራም ገንቢና በተጨባጭ ድክመቶች ላይ የተመሰረተ፣ ስራን እንጂ ሰውን ማእከል ያላደረገ እንዲሆን ይደረጋል፣

## አንቀጽ ፷፭.

## የብልፅግና ወጣቶች ሊግ መሰረታዊ ድርጅት አመራሮች አሰራር

የአመራር ኮሚቴ ስብሰባና ግንኙነት እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

፩. አመራር ኮሚቴው በወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ይኖረዋል፡፡ በዚህ መሰረት፡-

ሀ. ከህዋስና ከንዑሳን ኮሚቴ የመጣለትን ሪፖርት፣ እንዲሁም ከበላይ አካል የሚወርድለትን እቅድና አቅጣጫ ላይ ውይይት ያደርጋል፣ ለህዋሳትና ለንዑሳን ኮሚቴ አቅጣጫ ይሰጣል፣

፪. አመራር ኮሚቴው በሁሉም ጉዳዮች ላይ ያለውን ሃሳብ ለህዋሳት በአፋጣኝ ያሳውቃል፣

## አንቀጽ ፷፮.

## የንኡሳን ኮሚቴዎች አሰራር

፩. ሁሉም ንዑሳን ኮሚቴዎች በየሁለት ሳምንቱ መደበኛ ስብሰባ ይኖራቸዋል፣

፪. በስብሰባው ያለፈውን የስራ አፈፃፀም ይገመግማሉ፣ የቀጣይ ፲፭ ቀናት የስራ እቅድ በማፅደቅ ስራዎችን ተከፋፍለው ስምሪት ያደርጋሉ፣

፫. ለመሰረታዊ ድርጅት የሚቀርብ ሪፖርት ያዘጋጃሉ፣ ያቀርባሉ፣

፬. ለህዋሳት ኮሚቴ አቅጣጫዎችን ያወርዳል፣

## አንቀጽ ፷፯.

## የመሰረታዊ ድርጅት አመራር ከወጣቶች ሊግ ጽ/ቤት ኮሚቴ ጋር የሚኖረው ግንኙነት

፩. ሰብሳቢው ከሊግ ጽ/ቤት ኃላፊ ጋር እና ከኮሚቴ ሰብሳቢ ጋር የስራ ግንኙነት ያደርጋል፣

፪. የሊግ ጽ/ቤት ወይም ኮሚቴ አመራሩ በ፫ ወር አንድ ጊዜ የወጣቶች ሊግ መሰረታዊ ድርጅት ሰብሳቢና ምክትል ሰብሳቢ፣ ፀሀፊና የፋይናንስ ንዑስ ኮሚቴ ሰብሳቢዎችን አንድ ላይ ወደ ማእከል በመጥራት የስራ ግምገማ ይደረጋል፡፡ የዚህ ግንኙነት ዝርዝር አተገባበር ስለአመራር የግንኙነት ከላይ በተገለፀውና ውስጥ በሰፈረው አግባብ መሰረት ይፈፀማል፣

፫. እንደየአስፈላጊነቱ በየደረጃው ያሉት የሊግ ጽ/ቤት አመራሮች ከመሰረታዊ ድርጅት አመራር አባላት ጋር

መደበኛ የስራ ግዚያቸውን በማይጋፋና ለነሱ አመቺ በሆነ ጊዜ የጋራ ስብሰባ ያደርጋሉ፣

፬. ከበላይ አካል የሚሰጠውን እቅድና ልዩ ልዩ መመሪያ ቆጥሮ ይቀበላል፡፡ እቅዶችን ለተፈፃሚነት ያዘጋጃል፣

፭. ለበላይ አመራር የሚቀርብ ትችት ካለው በዚህ መድረክ በመጠቀም ያቀርባል፣

፮. በየሶስት ወሩ የተሟላ የስራ አፈፃፀም ሪፖርት ለሊግ ጽ/ቤት ወይም ለኮሚቴ ይልካል፣

## አንቀጽ ፷፰.

### የብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ የህዋሳት አደረጃጀት

፩. የሊጉ መሰረታዊ ድርጅት ለአባላት የዕለት ተዕለት ግንባታ የሚጠቀሙበት የህዋስ አደረጃጀት ይኖራቸዋል፡፡ የህዋስ አባላት ቁጥር ከ፲፩-፴፭ ይሆናል፣

፪. የሊጉ ህዋሳት የሚመሰረቱት ሙሉ አባላትን በመያዝ በመኖሪያ አካባቢ እና በስራ ቦታ ሆኖ በሚከተለው መልኩ ይሆናል፣

ሀ. የመንግስት ሰራተኞች /በፌደራል፣ በክልል፣ በዞን፣ በከተማ፣ በወረዳ/ልዩ ወረዳና በቀበሌ መስሪያ ቤቶች/ የሚሰሩ በተቋም ወይም በየዘርፉ ማለትም ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ አስተዳደራዊ ዘርፎችን መሰረት አድርገው ይደራጃሉ፣

ለ. የመምህራን፣ አስተዳደር ሰራተኞችና የተማሪዎች ህዋስ አመቺ በሆነበት ቦታ /ተቋም፣ በወረዳ፣ በቀበሌ/ ደረጃ ይደራጃል፣

መ. የሆስፒታል አባላት እንደ አመቺነቱ በሚሰሩበት ተቋም፣ ወረዳ/ቀበሌ ደረጃ ይደራጃሉ፣

ረ. የገጠር አርብቶና አርሶ አደሮች ህዋሳት መንደር/ቀጠናን መሰረት በማድረግ ይደራጃሉ፡፡

ሰ. በገጠር የተሰማሩ የመንግስት ሰራተኞች ህዋሳት የገጠር ባለሙያዎች እና በሌሎች ስራ የተሰማሩትን ባካተተ መልኩ የስራ ቦታ ወይም ቀበሌን መሰረት በማድረግ ይደራጃሉ፡፡

ሸ. የከተማ ነዋሪዎች ህዋሳት የመኖርያ ቦታን መሰረት በማድረግ በቀበሌ፣ በመንደር፣ በቀጠና ወይም በወረዳ ደረጃ ይደራጃሉ፡፡

ቀ. የከተማ ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት አባላት በተሰማሩበት የስራ ዘርፍ የሚደራጁ ሆኖ ቁጥራቸው አነስተኛ ከሆነ በአቅራቢያቸው ካለ ህዋስ ጋር ይደራጃሉ፡፡

በ. የላብአደር አባላት በስራ ቦታቸው በወጣቶች ሊግ ህዋስ ይደራጃሉ፡፡

ተ. በክልል መንግስታት ወይም በህዝብ ባለቤትነት የተያዙ የልማት ድርጅቶች የሚገኙ አባላት እንደ አመቺነቱ በሚኖሩበት ቀበሌ ወይም በአቅራቢያቸው ባሉ ተቋማት አደረጃጀቶች ውስጥ ታቅፈው በወጣቶች ሊግ ህዋስ ያደራጃሉ፡፡

፫. በአንድ ተቋም የሚሰሩ አባላት ቁጥራቸው ከ፲፩ በታች ከሆነ ከሌሎች ተቋም ጋር በክላስተር ይደራጃሉ፣

፬. ሁሉም አባል በህዋስ ተደራጅቶ መንቀሳቀስ ይጠበቅባቸዋል በአንድ የስራ ቦታ ወይም መኖሪያ የአባላት ቁጥር ከ፴፭ በላይ ከሆነ ሌላ ህዋስ መደራጀት ይቻላል፣

፭. እያንዳንዱ የወጣቶች ሊግ ህዋስ የራሱን አመራር ኮሚቴ ይመርጣል እነዚህም፡-

ሀ. ሰብሳቢ

ለ. የፖለቲካ ኃላፊ

ሐ. የአደረጃጀት ኃላፊ

መ. የፋይናንስ ጉዳይ ይሆናሉ

፮. ለወጣቶች ሊግ ህዋስ አመራርነት የሚመረጡ አባላት የሚያሟሉት መመዘኛ ከላይ ለመሰረታዊ ድርጅት አመራርነት የሚመረጡ በደረጃው ማሟላት የሚገባቸው መስፈርቶች ተመሳሳይ ይሆናል፡

## አንቀጽ ፷፱.

## የብልጽግና ፓርቲ የወጣቶች ሊግ ህዋስ ተልዕኮ

፩. አባላት በቀበሌያቸው/በወረዳቸው በመስርያ ቤታቸው ውስጥ በሚካሄዱ ብልፅግናን እና የወጣቶችን እኩልነት፣ ተሳትፎና ተጠቃሚነት የሚያረጋግጡና የሰላም ተግባራት ግንባር ቀደም ሆነው እንዲንቀሳቀሱ ማብቃት በዚህ ሂደትም አባላትን በተግባር እንዲገነባ ይደረጋል፣

፪. በህዋሱ ውስጥ የታቀፉትን አባላት በሙሉ በየግላቸው የሚያዘጋጁትን የግል እቅድ ማፅደቅ፣ አፈፃፀሙን መከታተል፣ መደገፍና ውጤቱን መገምገም፣

፫. የአባላትን የፖለቲካዊና ድርጅታዊ ብቃት እንዲኖራቸው ይሰራል፣

፬. የግንባር ቀደም ወጣቶችን አዳዲስ አባላት በመመልመል የብልፅግና ፓርቲ አባል በማድረግ ወደ ሊጉ በመቀላቀል የተደራጀ ጠንካራ እንቅስቃሴ እንዲኖራቸው ይደረጋል፣

## አንቀጽ ፸.

## የብልጽግና ፓርቲ የወጣቶች ሊግ ህዋስ አሰራር

ህዋሶች የሚከተለው ውስጣዊ አሰራር ይኖራቸዋል፡፡

፩. በየወሩ መደበኛ ስብሰባ ይኖራቸዋል፣

፪. የፖለቲካ ውይይት እና እያንዳንዱ አባል ብልፅግናን በሚያረጋግጡ ተግባራት ዙሪያ እንዲሁም የወጣቶች እኩልነት፣ ተሳትፎና ተጠቃሚነት ዙሪያ በግንባር ቀደምነት የሚያደርገው እንቅስቃሴ፣ የአባላትና የጋራ አደረጃጀት፣ በአጠቃላይም የአባላት እንቅስቃሴ የሚገመገምበት ይሆናል፣

፫. በግምገማው ላይ በመመስረትም የመማማር ፕሮግራም እንዲካሄድ ይደረጋል፣

፬. የህዋስ ስብሰባ የሚካሄደው ከአባላቱ ከግማሽ በላይ ከተገኙ ይሆናል፣

፭. ማንኛውም አባል በህዋስ ስብሰባ የመገኘት ግዴታ አለበት፣ አስገዳጅ በሆነ ሁኔታ ምክንያት የማይገኝ አባል አስቀድሞ የህዋሱን ሰብሳቢ ማሳወቅና ማስፈቀድ ይኖርበታል፡፡

## አንቀጽ ፸፩.

## የብልጽግና ፓርቲ የወጣቶች ሊግ ህዋሳት እንዲሁም የአመራር ኮሚቴና አባላት ተግባርና ኃላፊነት

፩. የህዋስ አመራር ኮሚቴ የሚከተለው ተግባራት ይኖረዋል፡፡

ሀ. የህዋሱን ሰብሳቢና ሌሎች ኃላፊዎች ይመርጣል፣

ለ. የህዋስ አባላት በተግባርና በአስተሳሰብ ግንባር ቀደም ሆነው በመንቀሳቀስ ላይ መሆናቸውን ይከታተላል፣

ሐ. ከመሰረታዊ ድርጅት የመጡ መመሪያዎችን የህዋሱ አባላት እንዲያውቋቸውና በአግባቡ እንዲፈፅሟቸው ያደርጋል፣ አፈፃፀማቸውንም ይቆጣጠራል፣

መ. አባላት ተልእኮቻቸውን ከመፈፀም አኳያ ያሉበትን ሁኔታ ይገመግማል፣ እያንዳንዱን አባል ዕቅድ በመገምገም ያፀድቃል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፣ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፣ ውጤቱን ይገመግማል፣

ሠ. አዳዲስ አባላት መስፈርቱን አሟልተው መመልመላቸውን ያረጋግጣል፣

ረ. የህዋሱን የውይይትና የግምገማ ፕሮግራሞችን ያዘጋጃል፣ በህዋሱ በማፅደቅም ስራ ላይ ይውላል፣

ሰ. የህዋሱ የውይይት ፕሮግራም ሳይስተጓጎል የሚካሄድበትን ሁኔታ ለመፍጠር ትኩረት ሰጥቶ ይንቀሳቀሳል፡፡ የሌሎችን ህዋሳት መልካም ተሞክሮ በመቅሰም ህዋሱ እንዲጠቀምበት ያደርጋል፣

ሸ. አመራር ኮሚቴው በየ፲፭ ቀኑ መደበኛ ስብሰባ በማድረግ መረጃዎችን ይለዋወጣል፣

ቀ. ለወጣቶች ሊግ መሰረታዊ ድርጅት በየወሩ ሪፖርት ይልካል፣

፪. የህዋስ ሰብሳቢዋ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖራታል፡፡

ሀ. የህዋሱን ስብሰባ በሰብሳቢነት ይመራለል፣

ለ. የህዋሱን ፖለቲካዊና አደረጃጀት ስራ በበላይነት ያስተባብራል፣

ሐ. ህዋሱን በመወከል ከመሰረታዊ ድርጅት አመራር ጋር ያገናኛል፣

መ. ህዋሱ ጠንካራ የተደራጀ ሆኖ እንዲንቀሳቀስ የሚያስችል አመራር ይሰጣሉ፣

ሠ. እያንዳንዱን የህዋስ አባል ፖለቲካዊ እንቅስቃሴውን ጠንካራና ደካማ ጎን በመለየት ድጋፍ እንዲያገኝ ያደርጋል፣

፫. የህዋሷ ፖለቲካ ኃላፊ የሚከተለው ተግባርና ኃላፊነት ይኖራታል፡፡

**ሀ.** የአባላትን ፖለቲካዊ ዝንባሌ ተከትሎ በማወቅና ሪፖርት በማድረግ ተገቢውን ፖለቲካዊ ግንባታ እንዲያገኙ ያደርጋል፤

ለ. እያንዳንዱ የሊግ አባላት የማስፋት ስትራቴጂው ተሳታፊና ተጠቃሚ ከመሆን አኳያ ያለበትን የግንዛቤና የቁርጠኝነት ሁኔታ በመከታተል ተገቢውን ድጋፍ እንድያገኝ ያደርጋል፤

ሐ. ህዋሳት እንዲወያዩበት ከበላይ አካል የሚመጣውን አጀንዳ እየተከታተለ ህዋሱ እንዲወያይበት ያደርጋል፡፡ አጀንዳውን በየርዕሱ ከፋፍሎ ማቅረብ አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ለህዋሱ አባላት አጀንዳውን ያከፋፍላል

የውይይት ፕሮግራም ያወጣል፤

መ. ከመሰረታዊ ድርጅት አመራር ጋር በመገናኘት ጋዜጣ/የመወያያ ርዕስ በወቅቱ እንዲደርስ ያደርጋል በወቅቱ ካልደረሰ ፈጥኖ ሪፖርት ያደርጋል እንዲሁም በወቅታዊ አጀንዳዎች እንዲወያዩ ያደርጋል፤

ሠ. የህዋስ አባላት ውይይትን ቃለ–ጉባዔ ይይዛል። በውይይት ወቅት የተነሱ አከራካሪና ልዩነት የተፈጠረባቸውን በሚገባ ሊጨበጡና ማብራሪያ የሚሹ ሀሳቦችን በመመዝገብ ይይዛል።

ረ. ለመሰረታዊ ድርጅቱ የፖለቲካ ስራ ሃላፊ በየወሩ ሪፖርት ያቀርባል፤

ሰ. ተጠሪነቱ ለህዋሱ ሰብሳቢ ይሆናል።

4. የአደረጃጀት ጉዳይ ኃላፊ የሚከተለው ተግባርና ኃላፊነት ይኖራታል።

ሀ. ህዋሷ ጠንካራ ሆና እንድትንቀሳቀስ የሚያስችል አመራር ይሰጣል፤

ለ. እያንዳዱ አባል በአደረጃጀትና አሰራር መመሪያዎች ላይ ያለውን ግንዛቤ ማጎልበትና በስራ ላይ እንዲይውል ይከታተላል፣ አመራር ይሰጣል፣

ሐ. የህዋሱን አባላት ማህደር ይይዛል፣ ሲያስፈልግም ለመሰረታዊ ድርጅቱ ያስተላልፋል፣

መ. የአባላት የመማማር ሂደት ቃለ–ጉባኤ ይይዛል፣ ውጤቱን በእያንዳንዱ አባል ማህደር ያሰፍራል፣

ሠ. ለመሰረታዊ ድርጅት አደረጃጀት ኃላፊ በየወሩ ሪፖርት ያቀርባል፣

ረ ተጠሪነቱ ለህዋሱ ሰብሳቢና ለመሰረታዊ ድርጅቱ የአደረጃጁት ኃላፊ ይሆናል።

5. የህዋሱ ፋይናንስ ጉዳይ የሚከተለው ተግባርና ኃላፊነት ይኖራታል።

ሀ. የአባላትን መዋጮ ያቅዳል፣ ከፓርቲው የፋይናንስ /ገንዘብ ያዥ ጋር በመቀኛጀት ህጋዊ ደረሰኝ እንዲሰበሰብ በማድረግ ለመሰረታዊ ድርጅት ሪፖርት ያደርጋል፣

ለ. የልሳናትና የብልፅግና ወጣቶች ሊግ መፅሔት ሽያጭ ገንዘብ በማሰባሰብ ገቢ ያደርጋል፣

ሐ. ተጠሪነቱ ለህዋሱ ሰብሳቢና ለመሰረታዊ ድርጅት ፋይናንስ ኃላፊ ይሆናል፣

## አንቀጽ 72.

## የብልጽግና ፓርቲ የወጣቶች ሊግ የደጋፊዎች ቡድን አደረጃጀት

1. እያንዳንዷ የሊግ አባል በተሰማራችበት የስራ መስክ ይሁን መኖሪያ ቦታ በጋራ አብረው ለሚኖሩና ለሚሰሩ

አካላት የፓርቲንና የወጣቶች ሊግ ዓላማዎችና እንቅስቃሴ የማስረዳት ኃላፊነት ይኖርባታል።

2. በዚህ መሰረት እያንዳንዱ አባል በስራ እና መኖሪያ ቦታዋ ፓርቲዉን እና ወጣቶች ሊግን በእዉቀት፣ በገንዘብና በጉልበት መደገፍ የሚፈልጉ ፈቃደኛ ደጋፊዎች የማፍራትና የጋራ አደረጃጀት ፈጥሮ የመንቀሳቀስ ኃላፊነት አለባት፣
3. ከመኖሪያ ቤቱና መስሪያቤቱ ውጪ በደጋፊነት ለመደራጀት ፈቃደኛ የሆኑ ወጣቶች ካገኙ ደጋፊዎች በምኖሩበት ወይም በምሰሩበት አካባቢ ለሚገኝ ህዋስ ስሙ እንዲተላለፍና በአካባቢው እንዲደራጅ የማድረግ ኃላፊነት ይኖርባቸዋል፣
4. እያንዳንዱ ደጋፊ ለመሆን ፍቃደኝነቱን ያረጋገጠ ግለሰብ ከሚቀራረቡትና ከሚስማሙት ወጣቶች ጋር እንዲደራጅ ይደረጋል፣
5. የደጋፊዎች ቡድን በተደራጁበት የደጋፊዉ ቡድን አባላት በተመረጠ፣ ተቀባይነትና የተግባር መሪነት የተረጋገጠ መሪ የሚመራ ይሆናል።
6. በጥቅሉ ወጣቶች በአደረጃጀት ተደራጅተው የሚንቀሳቀሱ ወጣቶችን በደጋፊነት በመያዝ በተልህኮዎች ማብቃት እና ለልማት፣ለመልካም አስተዳደር እና ለሁለንተናዊ ተሳታፊነት እናተጠቃሚነት ማንቀሳቀስ።

## አንቀጽ 73.

## የብልጽግና ፓርቲ ወጣቶች ሊግ የደጋፊዎች ቡድን ተልዕኮ

1. የፓርቲው እና የወጣቶች ሊግ ደጋፊዎች ቡድን አዳዲስና አስፈላጊ የሆኑ ሀሳቦችን የሚያገኙበት መድረክ ሆኖ ያገለግላል፣
2. የፓርቲው እና የወጣቶች ሊግ ደጋፊዎች ለፓርቲው ሊያቀርቡ የሚፈልጓቸዉ ጉዳዮች፣ አስተያየቶች፣ መስተካከል ያለባቸዉ አመላከከቶችና አሰራሮች፣ የሚያቀርቡት ገንቢ ሐሳቦችና ነቀፌታዎች፣ ሲኖሩ የሚያመቻች መድረክ ሆኖ ያገለግላል፣
3. ፓርቲው እና ወጣት ሊጉ ከጠቅላላ ወጣቶችና ምሁራን ጋር የሚኖረዉን ግንኙነት የሚያስተሳስር መድረክ ሆኖ ያገለግላል፣
4. በሂደትና በሙሉ ፈቃዳቸዉ ወደ ፓርቲው እና ቀጥሎም ወደ ወጣቶች ሊግ የሚቀላቀሉ አዳዲስ ወጣቶች አባላት የዕጩ አባላት መመልመያ መድረክ ሆኖም ያገለግላል፣
5. ለፓርቲው እና ወጣቶች ሊግ የሚያስፈልገው የእዉቀት፣ ጉልበትና የገንዘብ ድጋፍ ተጨማሪ አቅም ሆኖ ያገለግላል።

## አንቀጽ 74.

## የብልጽግና ፓርቲ የወጣቶች ሊግ የአባላትና ደጋፊዎች ቡድን አሰራር

1. የደጋፊዎች ቡድን ከተመሰረተ በኋላ የስብሰባና የውይይት ጊዜ፣ ከብልጽግና ፓርቲ የወጣቶች ሊግ ያለው ግንኙነት፣ ሌሎችም የሚመለከት አሰራር ራሱ ይወስናል፣

፫. የአባላትና ደጋፊዎች ቡድን በፍላጎትና መግባባት የሚመሰርት ይሆናል፣

፬. የደጋፊዎች ቡድን አባላት የፓርቲው አባልሆነው በቀጣይም ወደ ሊጉ አባል መሆን በሚፈልጉበት ጊዜ ጥያቄያቸው በቀጥታ በአቅራቢያቸው ለሚገኝ ህዋስ ያቀርባሉ፡፡ ህዋሱ ያለውን ውሳኔ ይገልፅላቸዋል፣

፬. በእያንዳንዱ ህዋስ ስር የተደራጁ የደጋፊ አባላት ዝርዝር ማህደራቸው በሊጉ መሰረታዊ ድርጅት የአደረጃጀት ኃላፊ ይቀመጣል፡፡ በየጊዜው ይታደሳል፣

፭. የደጋፊዎች ቡድን አባላት አስተያየታቸው ለሚመለከተው አመራር ይሁን ለኮንፍራንስ መላክ ሲፈልጉ በአቅራቢያቸዉ ላለ የብልጽግና ፓርቲ የወጣቶች ሊግ መዋቅር ወይንም እንደ አስፈላጊነቱ ይመለከተዋል ብለዉ ለሚያምኑት የፓርቲ መዋቅር ማቅረብ ይችላሉ፣

፮. የደጋፊዎች ቡድን በተስማሙበት የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ስለቡድናቸው የስራ አፈፃፀም ነፃ ሁነው ይወያያሉ፡፡ የዉይይታቸዉን ውጤት በአቅራቢያቸዉ ላለና ለሚደግፋቸዉ የሊግ መዋቅር እንዲደርስ ይደረጋል፡፡

**ጥር ፳016 ዓ.ም**